


# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 7ኛ ክፍል



የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ለመጽሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ




ይህን መጽሐፍ ብዙ ተማሪዎች ስለሚገለገሉበት በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባዋል፡፡ የሚከተሉት 10 ነጥቦች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዞ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡

1. የመጽሐፉን ሽፋን በጠንካራ ወረቀት ወይንም በላስቲክ መሸፈን፡፡
2. መጽሐፉን ርጥበት በሌለበት ደረቅ ቦታ ላይ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፡፡
3. መጽሐፉን በቆሻሻ እጅ ያለማገላበጥና ገፆቹን ያለመግለጥ፡፡
4. በመጽሐፉ የሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ያለመሳልና ያለመጻፍ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገጽ መለያ ወይንም የንባብ ማረፊያ የሆነ እልባት በጠንካራ ክርታስ ሠርቶ መጠቀም እንጂ የቆሙበትን ቦታ ለማስታወስ ገፆቹን ደጋግሞ ያለማጠፍ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ አንድም ገጽ ሆነ ስዕል ገንጥሎ አለማውጣት፡፡
7. መጽሐፉ ቢገነጠል እንኳ በጥንቃቄ መልሶ በማጣበቂያ ማስተሽ ማያያዝ፡፡
8. መጽሐፉ ቦርሳ ውስጥ ሲከተት እንዳይታጠፍና እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በውሰት ሲሰጥ የተዋሰው ሰው በጥንቃቄ እንዲይዝ መንገር፡፡
10. መጽሐፉን በጥንቃቄ መግለጥ፣ ገፆቹ እንዳይገነጠሉና እንዳይወይቡ በጥንቃቄ መያዝ፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 7ኛ ክፍል

አዘጋጅ፡- ፐሪን ኢንተርናሽናል አማካሪ ድርጅት

ጸሐፊ፡- አቶ ሰይፉ ይልማ

የቴክኒካል አማካሪዎች፡- ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ

አርታኢ፡- አቶ የሻው ተሰማ

ግራፊክስ ዲዛይን፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

የምልክት ቋንቋ ስዕል፡- አቶ ካሌብ በለጠ

ሌሎች ስዕሎች፡- አቶ አሰፋ ጉታ

አስተባባሪዎች፡- ዶ/ር ጥላዬ ካሣሁን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ማውጫ


መግቢያ ——— 3

ምዕራፍ አንድ:

ተፈጥሮን ማድነቅ ——— 9

ምዕራፍ ሁለት፡

የቤተሰብ ምጣኔ ——— 15

ምዕራፍ ሦስት፡

የቁጠባ ባህል ——— 22

ምዕራፍ አራት፡

የሕጻናት መብቶች ——— 30

ምዕራፍ አምስት፡

ሱሰኝነት ——— 36

ምዕራፍ ስድስት፡

ተላላፊ በሽታዎች ——— 42

ምዕራፍ ሰባት፡

ኤችአይቪ/ኤድስ ——— 48

ምዕራፍ ስምንት፡

አካል ጉዳተኝነት ——— 54

ምዕራፍ ዘጠኝ፡

የታዋቂ አርቲስቶች ግለታሪክ ——— 60

ምዕራፍ አስር፡

ሥነ ግጥም ——— 66

# መግቢያ

ትምህርት እና ልማት የማይነጣጠሉ ሂደቶች ናቸው፡፡ ልማት ያለ ትምህርት ትምህርትም ያለ ልማት ለታሰበላቸው ዓላማ ሊውሉ አይችሉም፡፡ ይህን ለማለት የደፈርነው ትምህርት ለልማት ቁልፍ መሳሪያ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህች ፈጣንና ወደ አንድ መንደርነት በመቀየር ላይ ባለችው ዓለም ስኬታማ ኑሮ ለመምራትና ከሌሎች ሀገሮች እኩል ወይም ቀድሞ ለመጓዝ ትምህርት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ይህንንም ታሳቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ከጀማሪ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ መማሪያ መጽሐፍትን፣ መርጃ መሳሪያዎችንና ግብዓቶችን ላለፉት በርካታ ዓመታት በማቅረብ ሀገራችን በትምህርት ለበርካታ ዓመታት ከሌሎች ሀገሮች እኩል እንድትጓዝ የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ይህንንም ለማስቀጠልና ተግባራዊነቱንም ለማጠናከር የትምህርት ሚኒስቴር በየጊዜው የሀገሪቱን ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ እንደአስፈላጊነቱም ከዚህ ቀደም የተዘጋጁትን ያሻሽላል፡፡ ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከ 1971 ዓ.ም. ጀምሮ በአንድ የምልክት ቋንቋ መጽሐፍ (የአማርኛ ምልክት ቋንቋ መስማትና መናገር ለተሳናቸው ሀ መጽሐፍ) ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ሲማሩ እስከ 2000 ዓ.ም. ድረስ ቆይተዋል፡፡ እንዲሁም ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2007 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጲያ ምልክት ቋንቋ መዝገበ ቃላት ሲማሩ ቆይተዋል፡፡ ይህ የምልክት ቋንቋ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም ከጀማሪ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ሲማሩ የቆዩት በአንድ የምልክት ቋንቋ መጽሐፍ በመሆኑ የምልክት ቋንቋ የሚፈለገውን የቋንቋ ዕድገት ለማስመዝገብና በምልክት ቋንቋ በመግባባት ሌሎችን የትምህርት ዓይነቶች በሚፈለገው መንገድ ለማስተማር ዕንቅፋት ሲሆን ቆይቷል፡፡

እንግዲህ ይህ የሰባተኛ ክፍል የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ በማስተማሪያነት ሲዘጋጅ ከዚህ ቀደም ከተዘጋጁት ለየት ያለና በዓይነቱም የመጀመሪያ ነው፡፡ ተማሪዎች፣ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ መምህራን፣ የተማሪዎቹ ወላጆች፣ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችና ምልክት ቋንቋ ለመማር ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች የኢትዮጲያ ምልክት ቋንቋ ለመማርና ለማስተማር በዚህ መጽሐፍ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዋና ዓላማ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ሃሳብን የመግለጽና መልሶ የመቀበል ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት አስፈላጊነት የተማሪዎች የማዳመጥ የመናገር የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ በዕይታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና፣ እንደሌሎች የልሳን ቋንቋዎች ጽሑፍ ስለሌለው፣ የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ከላይ እንደተጠቀሰው የተማሪዎችን በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ የመግባባት ክሂል ማዳበር ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ እንደሌሎች ቋንቋዎች እንዲያድግና መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ በመግባባት በትምህርታቸው የሚፈለገውን ውጤት አምጥተው ሀገር ተረካቢና ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ የመምህራን ድርሻ የጎላ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህራን የተማሪው መጽሐፍና መምህሩ መምሪያ በሚገባ አንብበውና ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት ዝግጅት አድርገው ግልጽ ያልሆነላቸውንም በአቅራቢያቸው የሚገኝ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ባለሙያ በመጠየቅ ተማሪዎቻቸውን በሚገባ እንዲያስተምሩ ይጠበቃል፡፡

## ጠቅላላ የማስተማሪያ ዘዴዎች

በዚህ የኢምቋ ትምህርት መርሃ ግብር ኢምቋ በዕይታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑና በአሁኑ ወቅት ውጤታማ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር (Student Centered) በመሆኑ መምህራን ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ እንዲጠቀሙ ይመከራሉ፡፡ መምህራን አመቻች (facilitator) እንጂ አምባገነናዊ መሪ (dictator) መሆን የለባቸውም፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎች የኢምቋ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ሙያዊ ማመቻቸት እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ገለጻ፣ ጭውውት፣ ገጠመኝ ማቅረብ፣ ውይይት፣ ድራማ፣ የምልክቶች ትንተና፣ አንብቦ መረዳት፣ ወዘተ የተካተቱ በመሆኑ አብዛኛውን የመማር ማስተማር ጊዜው የሚከናወነው በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ይሆናል፡፡

መምህራን ለእያንዳንዱ ምዕራፍና ለእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ምቹ ይሆናል ያሉትን የማስተማሪያ ዘዴ እንዲመርጡ ይበረታታሉ፡፡ በመሆኑም ጠቅለል ባለ መልኩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማስተማሪያ ዘዴዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

- ሰርቶ ማሳየት
- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ውይይት (ተማሪዎች ሁለት ሁለት ሆነው እንዲወያዩ፣ ምንባብ እንዲያነቡ፣ ቃለ ምልልስ እንዲያቀርቡ፣ ወዘተ የሚደረግበት ዘዴ ነው)
- ጥያቄና መልስ (አጫጭር ጥያቄዎችና መልሶች)
- ድራማ/ጭውውት
- ገለጻ (ተማሪዎች ከቡድን ውይይት፣ ከጥንድ ውይይትና በግል ከሚያቀርቡት ገለጻ በተጨማሪ በመምህሩና በተጋባዥ እንግዳ የሚቀርብ ገለጻ ሁሉ ያጠቃልላል)
- ፈልጎ ማግኘት (ይህ ዘዴ የሚከናወነው በመምህሩ መሪነት ተማሪዎች አንድ ተግባር ከተመለከቱ በኋላ ቀጥሎ ያለውን እንዲሰሩ ወይም ፈልገው እንዲያገኙ የሚደረግበት ዘዴ ነው)
- የመወያያ ጥያቄዎች

## በመማር ማስተማሩ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

በማንኛውም በመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያውኩ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት አዘወትረው ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል፣ የተማሪዎች በዕድሜ አለመመጣጠን፣ የተማሪዎች በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ፍላጎት ማጣት፣ ከአንዳንድ ስርዓተ ጾታና ጎጂ ባህሎች ጋር በያያዘ የሚከሰቱ ችግሮች ወዘተ ሲሆኑ ኢምቋ በመማር ማስተማር ሂደት ደግሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ችግሮች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

- ♦ በኢምቋ የሠለጠነ መምህር አለመኖር፣
- ♦ በቂ ብርሃንና ምቹ መቀመጫ ያለው የመማሪያ ክፍል አለመኖር፣

- ሌሎች በኢምቋ ዙሪያ የተጻፉ አጋዥ መጻሕፍት አለመኖር፣

- ኢምቋ በራሱ ሙሉ ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ የሚወክሉ ምልክቶች አለመኖር፣

- ለኢምቋ ትምህርት የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን፣

- አንዳንድ ተማሪዎች ከሩቅ ቦታ ተጉዘው የሚመጡ በመሆናቸው፣ የማርፈድና ከክፍል የመቅረት ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡

## የቡድን አመሰራረትና አተገባበር

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በልሳን ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ቤቶች በኢምቋ የሚያስተምሩ መምህራን ወይም የሰለጠኑ የኢምቋ አስተርጓሚዎች ያሉበት ትምህርት ቤቶች የሉም፡፡ በመሆኑም በኢምቋ የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች በሚፈለገው መጠን ስለሌሉ በኢምቋ በሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ከሩቅ ቦታዎች ተጉዘው የሚመጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምናልባት በአንድ ክፍል ውስጥ ከ20 በታች ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ፣

* ቡድን በሚመሰረትበት ወቅት የተለያዩ ቡድኖችን መመስረት ይቻል ዘንድ የቡድኑ አባላት ከሶስት ባይበልጡ ጥሩ ነው፡፡

* የትምህርት አቀራረብ ፖሊሲው በአካቶ የትምህርት ሥርዓት የሚያስተምር ከሆነ በቡድን ምስረታ ወቅት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የልሳን ቋንቋ ከሚሰሙ ተማሪዎች ጋር እንደብዛታቸው እኩል እንዲቧደኑ ማድረግ፡፡

* ከሌሎች የተሻለ የምልክት ቋንቋ ክሂል ያለው ተማሪ የቡድን መሪ ሆኖ ሌሎችን እንዲያወያይ ማድረግ፡፡

* የቡድን ገለጻና ውይይት በሚቀርብበት ዐውድ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት፡፡

* የቡድኑ የውይይት ውጤት ለክፍል ተማሪዎች በሚቀርብበት ወቅት የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ የሚታዩበት እንዳይሆን ለሁሉም እኩል ዕድል በመስጠት ማሳተፍ፡፡

## የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች

ከዚህ በላይ እንደገለጽነው ኢምቋ በዕይታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከገለጻ ይልቅ ትግበራ ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም ኢምቋ ለማስተማር አይነተኛ መርጃ መሳሪያ የምንለው በኢምቋ የተካኑ (መስማት ተሳናቸው ቢሆኑ ይመረጣል) ግለሰቦችን መጋበዝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኢምቋ በማስተማር ሂደት የመማር ማስተማር ሂደቱን ያግዛሉ የሚባሉት መርጃ መሳሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

* የቪዲዮ ማጫወቻ

* የተለያዩ ፊልሞችን ድራማዎች (መስማት በተሳናቸው የተሰሩ ቢሆኑ ይመረጣል (Films and drama)
* ኮምፒውተር (የትምህርት ቤቱን፣ ICT መጠቀም ይቻላል)
* ፊልፕ ቻርት
* የተለያዩ ስእሎች
* ካርታዎች ወዘተ፡፡

## ማበረታቻ

ማበረታቻ የምንለው ተማሪዎች የተጠየቁትን ጥያቄ በአጥጋቢ ሁኔታ ሲመልሱ፣ የተሰጣቸውን የቡድን፣ የጥንድና የግል ሥራዎችን በሚገባ ሲሰሩ የቤት ሥራዎችንና የክፍል ሥራዎችን በተገቢው መንገድ ሰርተው ሲያቀርቡ ወዘተ ከቃል ማበረታቻ ጀምሮ የተለያዩ ሽልማቶችን እስከ መስጠት ያጠቃልላል፡፡

በክፍል ውስጥ በመምህሩ የሚቀርብ የቃል ማበረታቻ ተማሪዎች ለወደፊቱ የበለጠ እንዲሰሩ የሞራል ስንቅ እንደሚሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ሌሎች ማበረታቻዎች እንደ አስፈላጊነቱ በወሰነ ትምህርቱ አጋማሽና የትምህርት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ላይ ለተማሪዎች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## ውጤት አሰጣጥ

መምህራን ለተማሪዎቻቸው ውጤት በወቅቱ የማሳወቅና ግብረ መልስ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ መምህራን በሚያወጡት ፈተና ክብደትና ተማሪዎችን በሚያሸማቅቁ ንግግራቸው መታወቅ የለባቸውም፡፡ መምህራን ሊጠቀሙባቸው ከሚችሉ የቃል ማበረታቻዎች መካከል እጅግ በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጥሩ፣ ደህና፣ በዚሁ ቀጥል፣ ወዘተ ሲሆኑ ከዚህ በተቃራኒው ደነዝ፣ የማይገባው፣ ደደብ፣ አንተን ማስተማር ድንጋይ ላይ ውሃ ማፍሰስ ነው፣ ሰነፍ፣ ስሜት የሌለው፣ ወዘተ እያሉ ተማሪዎችን ሥነልቦና መጉዳት የለባቸውም፡፡

## የጣት ፊደል አጠቃቀም መመሪያ

በዓለም ላይ በሚገኙ በሁሉም የምልክት ቋንቋዎች የጣት ፊደል መጠቀም የተለመደ ሲሆን አጠቃቀሙም እጅን ከትከሻ ትይዩ አድርጎ ሊነበብ በሚችል ፍጥነት የሚፈለገውን ነገር ስም በመጻፍ ነው፡፡ የጣት ፊደላት የምልክት ቋንቋ አካል ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁሉም ሃሳብና ስሜት በጣት ፊደል ይወከላል ማለት አይደለም፡፡ የጣት ፊደላት የሚወክሉት ስያሜ የሌላቸውን የቦታና የግለሰብ ስሞች የሐይቅ፣ የወንዝ፣ የከተማ፣ የባህር ስሞች (proper nouns) የአንዳንድ የዱርና የቤት እንስሳት ስሞች፣ ወዘተ ነው፡፡

የጣት ፊደሎችን በጽሑፋችን ውስጥ ስንጠቀም የጣት ፊደላት መሆናቸውን ለመለየት በእያንዳንዱ ፊደል መሀል የጭረት (-) ምልክት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ “ራስ ዳሽን ተራራ” ለማለት

ስንፈልግ "ራስ ዳሽን "የሚለውን ሐረግ የሚወክል ምልክት ስለሌለው ራ-ስ- ዳ-ሽ-ን ብለን ስንጽፍ በጣት ፊደል እንደተወከለ መረዳት ያስፈልጋል።

## የዓረፍተ ነገር አመሰራረት

በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ መልመጃዎች አሉ። ከነዚህ መልመጃዎች አንዱ ተማሪዎች ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያደርገው ክፍል ነው። ከወሊድ ጀምሮ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ትክክለኛ የስዋስው ሥርዓት የጠበቁ የአማርኛ ዓረፍተ ነገሮች ላይመሰርቱ ይችላሉ። የነዚህ መልመጃዎች ዓላማ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በኢምቋ የሚገልጿቸውን ሃሳቦች በጽሑፍ እንዴት እንደሚገለጹ ለማለማመድ ነው። በመሆኑም ከአማርኛ የስዋስው ሥርዓት ይልቅ የዓረፍተ ነገሮች የምልክቶች አገላለጽ ላይ ትኩረት በማድረግ ያበረታቷቸው።

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

በተማሪው መጽሐፍ በሁሉም ምዕራፎች ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ዓላማ ተማሪዎች ስለ ምዕራፉ ይዘት ያላቸውን እውቀት ለመለካትና በክፍል ውስጥ እኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማበረታታት ነው። በመሆኑም ከተቻለ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ እድል በመስጠት የማስተማሪያ ስልቱ ተማሪ ተኮር (student centered) እንዲሆን ያድርጉ።

## ግምገማ

ከእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ በኋላ መምህራን ተማሪዎቻቸውን መገምገም ይኖርባቸዋል። ተማሪዎችን ለመገምገም የሚያቀሙባቸው ዘዴዎች ውስጥ ተከታታይ ምዘና የምንለው ነው። ተከታታይ ምዘና መምህራን ተማሪዎቻቸውን በየጊዜው በመገምገም ትክክለኛ ውጤት እንዲይዙ ከማስቻሉም በተጨማሪ፣ ስለ ተማሪዎቻቸው የኢምቋ ክሂል ትክክለኛ መረጃ እንዲኖራቸው ያግዛል። በመሆኑም መምህራን ተመጣጣኝ የሆኑ የግምገማ ዘዴዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቻቸውን በየጊዜው መገምገም እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የግምገማ ዘዴዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይመከራል።

- የክፍል ተሳትፎአቸውን፣
- በድራማ/በጭውውት ትክክለኛ መልዕክት ማስተላለፋቸውንና ትክክለኛ ኢምቋ መጠቀማቸውን፣
- የቀረቡላቸውን ምንባቦችና ገለጻዎች የያዙዋቸውን ሃሳቦች መረዳታቸውን፣
- ምልክቶችን በትክክል መተንተናቸውን፣
- የኢምቋ አገባብ መጠቀማቸውን፣
- በቡድን፣ በጥንድና በግል ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረጋቸውን፣
- የቤትና የክፍል ሥራዎቻቸውን በጊዜው መስራታቸውን መገምገም ይኖርባቸዋል።

## የመገምገሚያ ዘዴዎች

የምልክት ጥያቄዎች(በልሳን ቋንቋ የቃል ጥያቄ የምንለው ነው)

- ድንገተኛ ሙከራዎች (ለተማሪዎች ሙከራ መኖሩን ሳንነግራቸው የምንገመግምበት ዘዴ ነው)
- የቡድን ሥራ፣
- የቤት ሥራ፣
- የክፍል ሥራ፣
- የወሰነ ትምህርቱ አጋማሽ ፈተና፣
- የማጠቃለያ ፈተናዎች፣

## የክፍለ ጊዜ ብዛት

በአብዛኛው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ቤቶች በሁለተኛ ሳይክል (ከ5ኛ-8ኛ ክፍል) የትምህርት ክፍሎች ለኢምቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት በአብዛኛው በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ነው። ይህንንም ታሳቢ በማድረግ ፡

- እያንዳንዱ ምዕራፍ 8 (ስምንት) ክፍለ ጊዜ እንዲይዝ ሲደረግ፣

እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ደግሞ 45 ደቂቃዎችን ይይዛል።

# ምዕራፍ አንድ

# ተፈጥሮን ማድነቅ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለ ተፈጥሮ ምንነት በኢትዮጲያ ምልክት ቋንቋ (ኢምቋ) ይገልጻሉ፤
- ስለ ተፈጥሮ ምንነት በኢምቋ ይወያያሉ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ መስህቦችን ይዘረዝራሉ፤
- ስለ ተፈጥሮ የቀረበላችሁን ምንባብ አንባችሁ ፍሬ ሃሳቦችን በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ከተፈጥሮ ማድነቅ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም በምልክት ቋንቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- ተፈጥሮ ከማድነቅ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ።

የማስተማሪያ መሳሪያዎች

ለዚህ ምዕራፍ ማስተማሪያነት መምህራን ካርታዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ጽሑፎች ልምድ ያላቸው የኢምቋ ባለሙያዎችን መጠቀም አለባቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ተፈጥሮን ከማድነቅ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን የተፈጥሮ መስህቦችና የተፈጥሮ ክስተቶችን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

በቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎች ስለ ተፈጥሮ ያላቸውን ዕውቀት ይመዝኑ፡፡ የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምንባቡ ውሥጥና በተለያዩ የምዕራፉ ክፍሎች ስለተካተቱ በጥያቄዎቹ ተማሪዎች የሚያውቁትንና የመሰላቸውን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

ስለ አስደናቂ ተፈጥሮዎች የቀረቡትን የተለያዩ ምንባቦች በኢምቋ በጋራ እንዲያነቡና የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በምልክት ቋንቋ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱ የውሃ አካላት አራት ሲሆኑ እነሱም የጣና ሐይቅ፣ የአባይ ወንዝ፣ የሀዋሳ ሐይቅና የገፈርሳ ሐይቅ ናቸው፡፡
2. የአባይ ወንዝና የጣና ሐይቅ  በኢትዮጲያ ውስጥ በአማራ ክልል  ይገኛሉ?
3. በራስ ዳሽን ተራራ ላይ የሚኖሩ እንስሳት ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ቀይ ቀበሮ፣ ዋሊያ፣ አቦሸማኔ፣ ቀጭኔ፣ ነብር፣ የሜዳ አህያ፣ የተለያዩ ወፎች፣ ወዘተ ይኖራሉ፡፡
4. በደቡብ ኢትዮጲያ ውስጥ የሚገኙ አስደናቂ ተፈጥሮዎች የሀዋሳ ሐይቅና የጢያ ትክል ድንጋዮች ናቸው፡፡
5. በአፋር ክልል የሚገኝ በአለም ላይ እጅግ በጣም አስደናቂ የሆነ የእሳት ባህር ኤርታሌ ተብሎ ይጠራል፡፡

6. ራስ ዳሽን ተራራ በኢትዮጵያ ውስጥ በአማራ ክልል ይገኛል።

## ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

1. የጣት ፊደል በጽሑፍ የሚወከለው በእያንዳንዱ ፊደል መሃል ጭረት(-) በማድረግ ነው።

ለምሳሌ፡

- እኔ ከ-በ-ደ እባላለሁ።
- ወንድሜ ባለፈው ዓመት ራ-ስ ዳ-ሽ-ን ተራራን ጎበኘ።

2. በምልክት ቋንቋና በአማርኛ ቋንቋ መካከል ያለው ልዩነት የምልክት ቋንቋ በእጅ፣ በፊት፣ በሰውነት እንቅስቃሴየሚገለጽ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ ደግሞ በልሳን የሚነገር መሆኑ ነው።
3. በምልክት ቋንቋ እና በአማርኛ ቋንቋ መካከል ያለው ተመሳሳይነት ሁለቱም የየራሳቸው የስዋስው ሥርዓት ያላቸውና ሃሳባችንን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው መሆናቸው ነው።
4. በምልክት ቋንቋ ሁሉም የምልክት ንዑስ ክፍሎች (parameters) መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ለምሳሌ እናት በሚለው ምልክትና አባት በሚለው ምልክት መካከል ያለው ልዩነት እጅ ቅርጹ በሚያርፍበት ቦታ ነው (አባት የሚለውን ምልክት ለመስራት እጅ ቅርጽ የሚያርፈው ግንባር ላይ ሲሆን እናት የሚለው ምልክት ደግሞ አገጭ ላይ ነው።)

## ከመልመጃ ሶስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው።

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

1. *ተራራ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “S” እና “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ግራ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከትከሻ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኙ “S” እጅ የግራውን “S” እጅ አይበሉባ መትቶ ወደ ላይ |

| | |
|---|---|
| | ሁለቱንም እጅ በመዘርጋት "ገ" መስራት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ዐይን በስተግራ ወደ ላይ ያያል |

2. *ባህር*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኙ እጅ "5" ቁጥር በግራ እጅ ደግሞ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የግራው ወደ ቀኝ የቀኙ ደግሞ ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የግራው እጅ በሰያፍ አጋድሞ የቀኝ እጅ ጣቶችን እያርገበገቡ በአመልካች ጣት በኩል የግራውን እጅ መዳፍ መንካት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

3. *ዋሊያ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "ወ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ሁለቱም እጆች ጭንቅላት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ከጭንቅላት ላይ አንስቶ ወደ ላይ በማድረግ ትንሽ ወደ ኋላ ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

4. *ቀበሮ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ "ሠ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | አፍንጫ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | አፍንጫን በአመልካች ጣትና በአውራ ጣት መካከል አስገብቶ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

5. *ሸለቆ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ቀኝ ግራው ወደ ግራ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ |

| | |
|---|---|
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱንም "ገ" እጅ ዘቅዝቆ የጉድጓድ ምልክት መሥራት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

6. *እሳተ ጎመራ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "0" እና "5" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከፊት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም እጅ ዘቅዝቆ "0" በመስራት ወደ ላይ ገልብጦ መዳፍን ወደ ውስጥ በማድረግ "5" ቁጥር መስራት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ጉንጭ ይወጠራል |

7. *ደሴት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "ደ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱም "ደ" እጆች ከሆድ ትይዩ አድርጎ ክንድን በመዘርጋት ወደ ሆድ በሁለቱም እጆች ክብ መሰራት፡፡ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም፡፡ |

8. *ሜዳ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "S" እና ገ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኙ "S" እጅ የግራውን "S" እጅ አይበሉባ መትቶ መዘርጋት (ገ መስራት) |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

9. *ዝንጀሮ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "S" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ደረት ላይ |

| | |
|---|---|
| የእጅ እንቅስቃሴ | እያፈራረቁ ደረትን መምታት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ምላስን የላይኛው ከንፈር ድድ ውስጥ በማስገባት የላይኛው ከንፈርን ወደ ፊት መወጠር |

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ አንብቦ መረዳት

በዚህ ክፍል ትምህርት ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ። እርስዎም ተማሪዎች በትክክል እንዲያነቡ እገዛ ያድርጉላቸው።

### መልመጃ አምስት፣ የቡድን ውይይት

ተማሪዎች ከምንባቡ ውስጥ ያገኙትንና ትክክል ነው ብለው ያመኑበትን የቡድን ውይይት ማቅረብ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ትክክለኛ ምልክት ቋንቋ መጠቀማቸውንና ትክክለኛ መልዕክት ማስተላለፋቸውን ይከታተሉ።

# ምዕራፍ ሁለት
# የቤተሰብ ምጣኔ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለቤተሰብ ምጣኔ ትርጉምና ጽንሰ ሃሳብ በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- የቤተሰብ ምጣኔ በግልም ሆነ በሀገር ደረጃ የሚያስገኘውን ጥቅም ይገልጻሉ፤
- የቤተሰብ ምጣኔ ለሀገር እድገት ያለውን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፤
- ስለ ቤተሰብ ምጣኔ የክርክር ሥርዐት ጠብቀው ይከራከራሉ፤
- የቤተሰብ ዕቅድ ትርጉምና ጽንሰ ሃሳብ ያብራራሉ፤
- በቤተሰብ ዕቅድ ሳቢያ የሚከሰት የእናቶችና የሕፃናት ጤንነት ጠንቆች በኢምቋ ይዘረዝራሉ፤
- የቤተሰበ ዕቅድ ለእናቶችና ለሕፃናት ጤንነት ያለው ጠቃሜታ ይገልጻሉ፤
- የቤተሰብ ዕቅድ ኘሮግራም ለሀገር ዕድገትና ልማት ያለው አስተዋጽኦ ይወያያሉ፤
- ከቤተሰብ ምጣኔ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም በም/ቋንቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- ከቤተሰብ ምጣኔ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከቤተሰብ ምጣኔ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ ሁለት የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን የቤተሰብ ምጣኔን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍል ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ

ለቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሚያውቁትን መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ በቅድመ ምንባብ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ በምዕራፉ ስለሚያገኙ ተማሪዎች አጠቃላይ ምዕራፉን በጽሞና እንዲከታተሉ ያበረታቷቸው፡፡

## ከቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች የሚጠበቁ መልሶች፡፡

1. ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፣ አጎት፣ አክስት፣ የወንድም ልጆች፣ የእህት ልጆች፣ ወዘተ ማለት ነው፡፡
2. የቤተሰብ ምጣኔ ማለት የሚወለዱት ልጆች ከቤተሰብ ገቢ ጋርና ከእናትየው ለመውለድ ከምትችልበት ሁኔታ ጋር ማገናዘብ ማለት ነው፡፡
3. አንድ ቤተሰብ ሊኖሩት የሚገባው የልጆች መጠን ከቤተሰቡ ገቢ ጋርና እናትየው ለመውለድ ካላት አቅም ጋር መገናዘብ አለበት፡፡ ምክንያቱም የቤተሰቡን ደህንነት የሚወስነው የልጆች መጠን ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ ገቢና የእናትየውና የተወለዱ ልጆች ጤንነት ሁኔታ ነው፡፡
4. ቤተሰብ መመጠን ለሀገር ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው ምክንያቱም ሀገር ማለት የቤተሰብ ድምር ውጤት ማለት ነው፡፡ ቤተሰብ ካልተመጠነ ጥራት ያለው ትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ ወዘተ ማግኘት ስለማይቻል ነው፡፡

## ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. የቤተሰብ ዕቅድ ማለት በልዩ ልዩ ባህላዊ ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሰራሽ የጽንስ መከላከያ ዘዴዎችን በመጠቀም ግለሰቦች ወይም ባልና ሚስት ወልደው ለማሳደግ የሚፈልጉትንና

የሚችሉትን ልጆች ብዛት እንዲሁም ለመውለድ የሚፈልጉበትን ጊዜ ራሳቸው በመወሰን የጠቅላላ ቤተሰቡን ደኅንነት ለመጠበቅ ማቀድ መቻል ማለት ነው፤

2. የዓለም ጤና ድርጅት የቤተሰብ ዕቅድ ከተነተነባቸው መንገዶች መካከል፤

- የማይፈለግ እርግዝናን መከላከልና የሚፈለግ ዕርግዝናን መቀበል
- ለመውለድ የሚፈልጉትን የልጆች ብዛት መወሰን በተከታታይ በሚወለዱ ልጆች መካከል ሊኖር የሚገባውን የጊዜ ልዩነት /የዕድሜ ልዩነት/ ማቀድ
- ለመውለድ የሚፈልጉትን ልጆች ብዛት ለማሳደግና ለቁም ነገር ለማብቃት ከሚያስችለው አቅም ወይም ከቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ /ገቢ/ ደረጃ ጋር ማገናዘብ እና
- ለመውለድ ማቀድ ናቸው፡፡

3. ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለጽ የቤተሰብ ዕቅድ የሚያተኩርባቸው ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች

    - የእናቶችና የህጻናት ጤንነት መጠበቅ
    - የህዝብ ቁጥር እድገት መግታት/መቆጣጠር
    - ሰብዓዊና ግለሰብአዊ መብት መጠበቅ ናቸው፡፡

4. የቤተሰብ ዕቅድ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለመቆጣጠር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ቤተሰብ የየራሱን ቤተሰብ መጠን የሚወስን ከሆነ ሀገሪቷ የምትፈልገውን የህዝብ መጠን ለማግኘት ያስችላታል፡፡
5. የቤተሰብ ዕቅድ ብቻውን ለሀገርና ለቤተሰብ ዕድገት አይጠቅምም፡፡ ምክንያቱም የቤተሰብ ዕቅድ ከሀገሪቱ የልማት መርሃ ግብሮችና ፖሊሲዎች ጋር በጋራ መስራት ይኖርበታል፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

### ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች፡፡

1. በኢትዮጲያ ውስጥ ከእርግዝናና ልጅ ከመውለድ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ መቶ ሺህ ሕጻናት በሕይወት ከሚወልዱ እናቶች መካከል 871 እናቶች ይሞታሉ፡፡
2. በእርግዝናና በወሊድ ወቅት ሴቶችን ለሞት የሚያበቁ ሁኔታዎች የማህጸን መድማት/ከወሊድ በፊት መድማት ወይም ከወሊድ በኋላ በብዛት ከማህጸን በብዛት ደም መፍሰስ፤ ከወሊድ እስከ 6ኛ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ የማህጸን በበሽታ ሕዋሳት መበከልና የእርግዝና መመረዝ ናቸው፡፡
3. በአዳጊ ሀገሮች ከሚሞቱ እናቶች መካከል 50 በመቶ የሚሆኑት የሚሞቱት ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው፡፡

4. በኢትዮጵያ ስለ ጋብቻ የወጣው የሀገሪቱ ደንብ ሴቶች ባል ለማግባት ዕድሜአቸው ከ15 ዓመት በላይ እንዲሆን ይደነግጋል፡፡
5. በምንባቡ መሰረት የሴቶች ልጅ የመውለጃ እድሜ ከ15-49 ዓመት ነው፡፡
6. ጠንካራ ደስተኛና ጤነኛ ዜጋ ለማፍራት የቤሰብ እቅድ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ይረዳል፡፡
7. ግለሰቦችም ሆነ ቤተሰቦች ልጅ ለመውለድ ሲፈልጉ በቅድሚያበአካል; በሥነልቦና; በማኀበራዊና በእኮኖሚያዊ ዝግጅት ብቃት እንዲኖራቸውና የሚወልዷቸውን ለጆች ብዛትና መቼ መውለድ እንደሚፈልጉ አስቀድመው መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡
8. የእናቶች ጤንነት ተጠብቆ ሀገር ተረካቢና ብቁ ዜጋ እንዲያፈሩ እናቶች አራርቀው መውለድ; ድንገተኛ ውርጃ እንዳይከሰት መጠንቀቅ; ብርግዝና ወቅትና ጡት በሚያጠቡበት ወቅት የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ኖርባቸዋል፡፡

## ከመልመጃ ሶስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

1. *ውርጃ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የግራ እጅ “5” የቀኙ ደግሞ የጉርሻ ምልክት |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የግራው ወደ ታች የቀኙ ደግሞ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ሆድ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኝ የጉርሻ እጅ የግራ እጅ መዳፍ ነክቶ ወደታች እንደመጎተት አድርጎ ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

2. *መውለድ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ የታጠፈ “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ሆድ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም እጆች አነባብሮ ሆድ ላይ ካደረጉ በኋላ የቀኙን እጅ ወደ ታች ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

3. *ጤንነት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “ሠ” ወይም “9” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ትከሻ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በአመልካች ጣትና በአውራ ጣት ትከሻን ነክቶ ወደ ፊት መውሰድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

4. *ሕዝብ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “T” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ትይዩ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ /ከደረት ፊት/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በሁለቱም የ“T” እጅ እያፈራረቁ ወደ ላይና ወደ ታች ከፍና ዝቅ ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

5. *እርግዝና*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ የታጠፈ “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም እጆች ሆድ ላይ አድርጎ እኩል ወደፊት መግፋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ጉንጭ ይወጠራል |

6. *መከላከል*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ ‘’S’’ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከግራ ትከሻ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱን ''S'' እጆች አጋጥሞ ወደ ፊት መግፋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ኮሳተራል |

7. *መድማት/ደም*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "5" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | አፍንጫ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም እጆች አፍንጫ ላይ በማድረግ የቀኙን እጅ በግራ እጅ አይበሉባ በኩል ጣቶችን እያርገበገቡ ወደ ታች ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

8. *በሽታ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ "5" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ግራ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የጎን ግንባር ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በመሀል ጣት የጎን ግንባርን ነክቶ መጠምዘዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ይጨፈግጋል |

9. *ኢኮኖሚ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የግራ እጅ ገ የቀኙ ደግሞ ''E'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ /ከደረት ፊት/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የግራውን ገ እጅ መዳፍ በቀኙ ''E'' እጅ አይበሉባ መጠብጠብ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

10. *ማኅበራዊ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅሠ "ሠ" ወይም "9" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ/ከደረት ፊት |

| | |
|---|---|
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱን “ሡ” እጆች በአውራ ጣትና በአመልካች ጣቶች አቆላልፎ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*የመወያያ ጥያቄዎች*

ተማሪዎች ሦስት ሦስት ሆነው ከተወያዩ በኋላ የውይይታቸውን ፍሬ ሃሳብ በቡድን ተወካዮቻቸው አማካይነት ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የቁጠባ ባህል

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለ ቁጠባ ባህል ምንነት በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- የቁጠባ ባህል አስፈላጊነት ያብራራሉ፤
- የቁጠባ ባህል ጠቃሜታን በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ምን መቆጠብ እንዳለባቸው ይዘረዝራሉ እንዲሁም የቁጠባ ዓይነቶችን ይለያሉ፤
- ቁጠባ ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ እንዲሁም ለሀገር ዕድገት ያለው ጠቃሜታ ይዘረዝራሉ፤
- ከቁጠባ ባህል ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም በም/ቋንቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታላሉ፤
- ከቁጠባ ባህል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከቁጠባ ባህል ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ ሶስት የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን ቁጠባን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍል ትምህርት ሁለት: ማድመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምንባቡ ውስጥ ስለሚገኝና ተማሪዎች በክፍለ ትምህርቱ ስለሚመልሱት ለቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች የሚያውቁትንና የመሰላቸውን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. ገንዘብ መቆጠብ ዘመናዊ የአኗኗር ዘዴ ነው የምንልበት ምክንያት ገንዘብ የሚቆጥብ ግለሰብ ማንንም ሳያስቸጀግር በፈለገው ሰዓት በቆጠበው ገንዘብ የፈለገውን ማድረግ ስለሚችል ነው፡፡

*ዘመናዊ ቁጠባ ዘዴ ጠንካራ ጎኖች*

- ገንዘብ በፈለግነው ሰዓት ማስቀመጥ ይቻላል
- ገንዘብ በፈለግነው ሰዓት ወደፈለግነው ቦታ መላክ ይቻላል
- ተጨማሪ ወለድ ያስገኛል
- በሌባ ሊሰረቅ አይችልም

*ባህላዊ የቁጠባ ዘዴ ጠንካራ ጎኖች*

- የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ግንኙነት ያዳብራል፡፡
- በሀዘንና በደስታ ጊዜ ለመረዳዳት ያስችላል፡፡
- የህብረተሰቡን ባህል ያጠናክራል፡፡

- የማኅበረሰቡን ችግሮች ተወያይቶ ለመፍታት ያስችላል

*ዘመናዊ የቁጠባ ዘዴ ደካማ ጎኖች*

- ብዙም ደካማ ጎኖች የሉትም
- በፈለግነው ሰዓት ገንዘብ ማስቀመጥ አያስችልም
- በፈለግነው ሰዓት ካስቀመጥነው ላይ አውጥተን መጠቀም አንችልም

*ባህላዊ የቁጠባ ዘዴ ደካማ ጎኖች*

- በሌባ ሊሰረቅ ይችላል
- ወለድ አያስገኝም
- ካስቀመጥነው ላይ ወደ ፈለግነው ቦታ መላክ አንችልም

2. የባህላዊ የቁጠባ ዓይነቶች የሚባሉት ዕድርና ዕቁብ ናቸው፡፡
3. ተማሪዎች ጊዜአቸውን፣ የደንብ ልብሳቸውን (ዩኒፎርማቸውን)፣ ደብተራቸውን፣ ደብተር የመያዣ ቦርሳቸውን፣ ወዘተ ሊቆጥቡ ይችላሉ፡፡
4. ፈላስፋው ትንሽ ቀዳዳ ትልቁን መርከብ ታሰምጠዋለች ያለው ትንንሽ ወጪዎች የቤተሰብን ገቢ ይጎዳሉ፤ በተጨማሪም ትንንሽ ወጪዎች ለገንዘብ ብክነት ያጋልጣሉ ለማለት ነው፡፡

## ክፍል ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

### ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ ሦስት የሚጠበቁ መልሶች

1. ሐ

2. ሠ

3. ለ

4. መ

5. ሀ

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

1. *መንግስት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ በመጠኑ የታጠፈ “5” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | አናት/ ጭንቅላት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በታጠፈው “5” ቁጥር ጣቶች ጫፍ አናት ላይ ማስቀመጥ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

2. *ግለሰብ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “ሠ” ወይም “9” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ትከሻ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በአመልካችና በአውራ ጣት ጫፍ የትከሻችንን ጫፍ መያዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

3. *መርዳት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ “አ” የግራ እጅ ደግሞ “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ግራ የግራው ደግሞ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን “አ” እጅ በግራ “ገ” እጅ መዳፍ ላይ አስቀምጦ አንድ ላይ ወደ ላይ ከፍ ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

4. *መላክ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ የታጠፈ "ገ" የግራው ደግሞ "S" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከግራ ትከሻ ከፍ ብሎ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን "ገ" እጅ ጣቶች በግራ "S" እጅ አይበሉባ ላይ አድርጎ ወደ ላይ መዘርጋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

5. *ሀብት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ በመጠኑ የታጠፈ "5" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን "5" ቁጥር እጅ በግራ እጅ መዳፍ ላይ አስቀምጦ ወደ ላይ ከፍ ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

6. *ገንዘብ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጆች "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጅ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ መዳፍ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የግራውን "ገ" እጅ መዳፍ በቀኙ "ገ" እጅ አይበሉባ መጠብጠብ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

7. *ዕጣ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ የተቆለመመ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጅ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱም የተቆለመሙ "ገ" እጆች በትንሹ ጣት በኩል አጋጥሞ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

8. *መስረቅ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ “2” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ ክንድ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን “2” ቁጥር እጅ በግራ እጅ ክንድ ላይ አድርጎ ወደ ቀኝ በመሳብ መቆልመም |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

9. *ወለድ*

ወለድ ማለት ባንክ ቤት የተቀመጠ ገንዘብ ላይ ባንክ ቤቱ የሚያደርገው ጭማሪ በመሆኑ ገንዘብና መጨመር የሚሉትን ሁለት ምልክቶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

10. *ገቢ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ በመጠኑ የተቆለመመ “5” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ ብብት ውስጥ /የግራ ጎን ላይ/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን በመጠኑ የተቆለመመ እጅ የግራ ብብት ውስጥ ማስገባት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

*ተማሪዎች የተለያየ አገባብ ያላቸው የምልክት ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በታች የተሰጡት መልሶች አጋዥ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡*

1. መቀበል
    - ኤፍሬም እንግዳ ተቀበለ (እዚህ ላይ ማስተናገድ/መጋበዝ የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)
    - ቶላ ወንድሙ የላከለትን ገንዘብ ተቀበለ (እዚህ ላይ መውሰድ የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)

2. ማውጣት

- ገንዘብ ያለ ምክንያት ማውጣት ጥሩ አይደለም (እዚህ ላይ ማባከን የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)
- የሚረብሹ ተማሪዎችን ለይተን ማውጣት ያስፈልጋል (እዚህ ላይ መውጣት የሚለውን ምልክት መጠቀም ያስፈልጋል)

3. ወለድ

- የአጎቴ ልጅ አየር ወለድ ነው (እዚህ ላይ ወታደር የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)
- ባንክ ቤት የተቀመጠ ገንዘብ ወለድ ያስገኛል (እዚህ ላይ ጭማሪ የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)

4. መጥፋት

- ብዙ ወጣቶች ከሀገር እየጠፉ ወደ ሌላ ሀገር ይሄዳሉ (እዚህ ላይ መሰደድ የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)
- የህዳሴው ግድብ ሲጠናቀቅ የመብራት መጥፋት ችግር ይወገዳል (እዚህ ላይ መብራት ጠፋ የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)

5. ማስቀመጥ

- ገንዘብ ማስቀመጥ በጣም ጥሩ ነው (እዚህ ላይ መቆጠብ የሚለውን ምልክት መጠቀም ይቻላል)
- የመማሪያ ደብተርና መጽሐፎችን ጥሩ ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል (እዚህ ላይ መቀመጥ የሚለውን ምልክት መጠቀም ያስፈልጋል)

## ከመልመጃ ስድስት የሚጠበቁ መልሶች

*ተማሪዎች የተለያየ የግስ አረባብ ሊሰሩ ይችላሉ። ከዚህ በታች የተሰጡት መልሶች አጋዥ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል።*

1. መርዳት

ረዳ (እሱ እና መርዳት የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ረዳች (እሷ እና መርዳት የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ረዷ (መርዳት የሚለውንና ስም አመልካች ወይም ጨራሽ ምልክቶችን መሥራት)፣ ረዱ (እነሱና መርዳት የሚሉትን ምልክቶችን መሥራት)፣ ትረዳለች (እሷ፣ ወደፊት እና መርዳት የሚሉትትን ምልክቶች መስራት)፣ ይረዳሉ (እነሱ፣ ወደፊት እና መርዳት የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መስራት)፣ እንረዳለን (እኛ፣ ወደፊት እና መርዳት የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መሥራት)

2. መቀበል

ተቀበለ (እሱ እና መቀበል የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ተቀበለች (እሷ እና መቀበል የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ተቀባይ (መቀበል የሚለውንና ስም አመልካች ወይም ጨራሽ ምልክቶችን መሥራት)፣ ተቀበሉ (እነሱና መቀበል የሚሉትን ምልክቶችን መሥራት)፣ ትቀበላለች (እሷ፣ ወደፊት እና መቀበል የሚሉትትን ምልክቶች መስራት)፣ ይቀበላሉ (እነሱ፣ ወደፊት እና መቀበል የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መስራት)፣ እንቀበላለን (እኛ፣ ወደፊት እና መቀበል የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መሥራት)

3. መግዛት

ገዛ (እሱ እና መግዛት የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ገዛች (እሷ እና መግዛት የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ገዢ (መግዛት የሚለውንና ስም አመልካች ወይም ጨራሽ ምልክቶችን መሥራት)፣ ገዙ (እነሱና መግዛት የሚሉትን ምልክቶችን መሥራት)፣ ትገዛለች (እሷ፣ ወደፊት እና መግዛት የሚሉትትን ምልክቶች መስራት)፣ ይገዛሉ (እነሱ፣ ወደፊት እና መግዛት የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መስራት)፣ እንገዛለን (እኛ፣ ወደ ፊት እና መግዛት የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መሥራት)

4. መሸጥ

ሸጠ (እሱ እና መሸጥ የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ሸጠች (እሷ እና መሸጥ የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ ሻጭ (መሸጥ የሚለውንና ስም አመልካች ወይም ጨራሽ ምልክቶችን መሥራት)፣ ሸጡ (እነሱና መሸጥ የሚሉትን ምልክቶችን መሥራት)፣ ትሸጣለች (እሷ፣ ወደፊት እና መሸጥ የሚሉትትን ምልክቶች መስራት)፣ ይሸጣሉ (እነሱ፣ ወደፊት እና መሸጥ የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መስራት)፣ እንሸጣለን (እኛ፣ ወደ ፊት እና መሸጥ የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መሥራት)

5. ማምጣት

አመጣ (እሱ እና ማምጣት የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ አመጣች (እሷ እና ማምጣት የሚሉትን ምልክቶች መስራት)፣ አምጪ (ማምጣት የሚለውንና ስም አመልካች ወይም ጨራሽ ምልክቶችን መሥራት)፣ አመጡ (እነሱና ማምጣት የሚሉትን ምልክቶችን መሥራት)፣ ታመጣለች (እሷ፣ ወደፊት እና ማምጣት የሚሉትትን ምልክቶች መስራት)፣ ያመጣሉ (እነሱ፣ ወደፊት እና ማምጣት የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መስራት)፣ እናመጣለን (እኛ፣ ወደ ፊት እና ማምጣት የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መሥራት)

# ምዕራፍ አራት

# የሕጻናት መብቶች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የሕጻናት መብቶች ምንነት በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- የሕጻናት መብቶች መከበር ያለውን ጠቃሜታ ይዘረዝራሉ፤
- ስለ ሕፃናት መብቶች የሚገልጹ ሕገ መንግስታዊ አንቀጾችን ይለያሉ፤
- የሕፃናትን መብት በማስመልከት ጭውውቶች (ድራማዎች) ታቀርባላችሁ፤
- ከሕጻናት መብቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም በኢምቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- ከሕጻናት መብቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከህጻናት መብቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚያውቋቸውን የህጻናት መብቶችን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡ ፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ።

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ስለ ሕጻናት መብቶች የሚገልጸውን ምንባብ በጋራ አንብባችሁ በተማሪው መጽሀፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በኢምቋ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው።

1. ሕጻናት የመማር፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመመማር፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ፣ የልደት ምዝገባ ሰርተፍኬት የማግኘት መብቶች አሏቸው።
2. የሕጻናት መሰረታዊ መብቶች የሚባሉት አካላዊ ጥቃት እንዳይደርስባቸው የመጠበቅ፣ ከቤተሰብ ጋር የመገናኘት መብት፣ የመማር መብት ናቸው።
3. የሕጻናት መብቶች መከበር እንዳይጠለፉ፣ ጉልበታቸው እንዳይበዘበዝ፣ በነጻነት እንዲማሩና ብቁና ሀገር ተረካቢ ዜጋ እንዲሆኑ ያስችላል።
4. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱ ሕጻናት ሃሳባቸውን መግለጽ የሚችሉባቸው መንገዶች በንግግር፣ በጽሑፍና በስእል ናቸው።
5. ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት።
6. ሕጻናት ከመብቶቻቸው በተጨማሪ፣ ወላጆቻቸውን የማክበር፣ በትምህርት ቤት ውስጥ መምህራንን የማክበር፣ በትምህርት ሰዓት በትምህርት ክፍል ውስጥ የመገኘት፣ የመማሪያ መሳሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝ ግዴታዎች አሉባቸው።
7. በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት የሕጻናት መብቶች በተጨማሪ መስማት የተሳናቸው ሕጻናት በምልክት ቋንቋ የመግባባት በምልክት ቋንቋ የመማርና የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ የማግኘት መብቶች አሏቸው።

## ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በአምስት ቡድኖች ተከፍለው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በቡድን ውይይት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም በቡድን ተወካዮቻቸው አማካይነት የውይይታቸውን ፍሬ ሃሳብ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በዚህ አውድ የምልክቶችን አጠቃቀምና የመወያያ ርዕሶች ለተማሪዎች ግልጽ መሆኑ ላይ ትኩረት ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

## ከመልመጃ ሦስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

*1. ጭቆና*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ የጉርሻ ምልክት የግራው ደግሞ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደላይ የግራው ደግሞ ወደታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ/ ከደረት ፊት/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን የጉርሻ እጅ ጣቶችን በግራ እጅ መዳፍ ወደ ታች መጫን |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ይኮማተራል |

*2. ጸታ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ "ጸ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከጉንጭ ከፍ ብሎ/ ጆሮ ግንድ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በ "ጸ" እጅ ከጆሮ ግንድ ወደ ጉንጭ ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 3. ብሔር

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ "በ" በግራ እጅ ደግሞ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ እጅ ወደ ውጭ የግራው ደግሞ ወደታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ አይበሉባ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን "በ" እጅ አሽከርክሮ በግራ ''S'' አይበሉባ ላይ ማሳረፍ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 4. አድልዖ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ  "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ /ከሆድ ፊት/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ላይና ወደ ታች እንደ ሚዛን በማወዛወዝ አንዱ እጅን ወደታች ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | አገጭ ወደጎን ይጣመማል |

### 5. ስደት/መሰደድ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ እጅ "1" ቁጥር የግራው ደግሞ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ውጭ የግራው ደግሞ ወደታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ፊት/ ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን "1" ቁጥር እጅ በግራው "ገ" እጅ ጣቶች መሐል አስገብቶ የቀኙን እጅ ብቻ ወደ ቀኝ መውሰድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 6. ጎሳ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ "ገ" የግራው ደግሞ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ውጭ የቀኙ ደግሞ ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ አይበሉባ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን "ገ" እጅ አሽከርክሮ በግራ እጅ አይበሉባ ላይ ማሳረፍ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 7. ስቃይ/መጨነቅ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጅ ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ሆድ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱንም እጆች አንዱ ባንዱ ላይ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ዐይን በመጠኑ ይጨፈናል ፊት ይኮማተራል |

### 8. ግዴታ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ ''C'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከፊት በስተ ጎን/ ጆሮ ግንድ አካባቢ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ፊት መግፋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ይኮሳተራል |

### 9. መታዘዝ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የቀኝ እጅ ከፊት የግራ እጅ ደግሞ ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም እጆች እኩል ወደ ታች ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 10. ጠበቃ

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “ጠ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጅ ወደታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱንም ጠ እጆች አጋጥሞ ወደፊት መግፋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### ሀሳብን የመግለጽና የመቀበል ክሂል

በዚህ ክፍል ትምህርት ላይ ተማሪዎች ከተሰጣቸው ርዕስ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ድራማዎች (ጭውውቶችን) ሰርተው እንዲያቀርቡ ይንገሯቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# ሱሰኝነት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የሱሰኝነት ምንነት በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ሱሰኝነት የሚያስከትላቸውን የጤና፣ ማህበራዊ ኑሮና የሥነ ልቡና ችግሮችን በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ለሱሰኝነት አጋላጭ የሆኑ መንገዶችን በመለየት ይዘረዝራሉ፤
- ሱሰኝነትን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ይወያያሉ፤
- ከሱሰኝነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም በም/ቋንቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- ከሱሰኝነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከሱሰኝነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ አምስት የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን ሱሰኝነትን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍል ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምንባቡ ውስጥና በምዕራፉ የተለያዩ ክፍሎች የሚመለሱ በመሆናቸው ተማሪዎች ስለ ሱሰኝነት ያላቸውን ግንዛቤ ለመገመት የተዘጋጀ ነው፤ በመሆኑም ከምንባቡ በፊት ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በኢምቋ ያቅርቡላቸውና ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱ የሱስ የሱሰኝነት ዓይነቶች አምስት ሲሆኑ እነሱም ጫት መቃም ሺሻ ማጤስ/መሳብ ሲጋራ ማጤስ አልኮል መጠጥ አብዝቶ መጠጣት ቤንዚን ማሽተት ናቸው፡፡
2. ሰዎች ሱሰኛ የሚሆኑት በተሳሳተ አመለካት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ጫት መቃም ለጥናት ጥሩ ነው ብለው ስለሚያስቡ፣ ሲጋራ ማጤስ ዘመናዊነት ወይም መሰልጠን ስለሚመስላቸው፣ ሺሻ መጠቀም ቆዳ ያጠራል ሀሺሽ ደግሞ ደፋር ያደርጋል በለው ስለሚያስቡ፡፡
3. ሱሰኝነት የሚያስከትላቸው የኢኮኖሚ ችግሮች ለጫት፣ ለሲጋራ፣ ለሺሻ፣ ለሀሺሽ፣ ለአልኮል መጠጥ የሚወጣ ወጪ የቤተሰብ ገቢ ይጎዳል የጤና ችግር ስለሚያስከትል ለጤና ተብሎ የሚወጣው ወጪ የግለሰቡንም ሆነ የሀገር ኢኮኖሚ ይጎዳል በሱስ የተያዘ ሰው ሥራውን በአግባቡ ማከናወን ስለማይችል ግለሰቡም ሆነ ሀገሪቷ ማግኘት የነበረባቸውን ገቢ ሳይገኙ ይቀራሉ፡፡
4. ሱሰኝነት የሚያስከትላቸው የጤና ችግሮች የምንላቸው በሱስ የተያዘ ሰው አብዝቶ ሲጋራ ስለሚያጤስ፣ አልኮል ስለሚጠጣ የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽን፣ የሳንባ በሽታ፣ የጉበት በሽታ፣ የጨጓራ በሽታ፣ ወዘተ ናቸው፡፡
5. ሱሰኛ ሰው ማኅበራዊ ግንኙነቱ ደካማ ነው የምንልባቸው ምክንያቶች ቤተሰብ ይበትናል፤ ጊዜውንም በአግባቡ ስለማይጠቀምበት በማኅበራዊ ግንኙነቶች ላይ አይሳተፍም ከዚህ በተጨማሪም

የስራ ገበታው ላይ በአግባቡ ስለማይገኝ ከስራ መባረር ሊያስከትል ስለሚችል ለልመና አሊያም ለስርቆት ወንጀል ሊጋለጥ ስለሚችል ነው፡፡

6. አክሎግ የዘረዘራቸው ሱሰኝነት የሚያስከትላቸው የሥነ ልቡና ችግሮች በሱስ የተያዘ ሰው የአፉና የልብሱ ጠረን /ሽታ/ ስለሚቀየር፣ ኢኮኖሚው /ገቢው/ ስለሚጎዳ እንደ እድር፣ ሰርግ፣ እቁብ በመሳሰሉት ማህበራዊ ግንኙነቶች ስለማይሳተፍ ምናልባትም ቤተሰቡ ስለሚበተን ወዘተ ከፍተኛ ለሆነ የሥነ ልቡና ችግር ይጋለጣል፡፡

7. ሱሰኝነትን ለመከላከል ወይም በሱስ እንዳንያዝ ከጓደኛ ግፊት መራቅ/ሱስ ያለበት ጓደኛ አለመያዝ/ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦችን ማስወገድ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በሁሉም ቦታዎች ማስፋፋት፡፡

## ክፍል ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

### ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የአረፍተ ነገሮችን ሀሳብ ከተረዱት የአማርኛ ግሶች እንደ አገባባቸው የተለያዩ ምልክቶች እንዳሏቸው በተለያዩ ምልክቶች ሊያሳዩ ስለሚችሉ፤ በመሆኑም አረፍተ ነገሮቹ የያዙትን ሃሳብ መምህሩ ለተማሪዎች በማስረዳት ተማሪዎች የተለያዩ ምልክቶችን እንዲያሳዩ በማበረታታት ከተማሪዎች ጋር በጋራ የሚሰራ ነው፡፡

### ከመልመጃ ሶስት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች በመልመጃ ሁለት በተሰጡት ምሳሌዎች መሰረት የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም እንደአገባባቸው የሚለያዩ ኣረፍተ ነገሮችን እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

### 1. *በሽታ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “5” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ግራ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የጎን ግንባር ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የመሀል ጣትን ወደ ፊት በማውጣት የጎን ግንባር ላይ አድርጎ መጠምዘዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *2. ሥነ ልቡና/ሳይኮሎጂ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ “ገ” የግራው ደግሞ “ሀ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ግራ የግራው ደግሞ ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የግራውን “ሀ” እጅ መሀል በቀኙ “ገ” እጅ በሰያፍ መጠብጠብ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *3. አልኮል መጠጣት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “አ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ግራ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከከንፈር ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | አውራ ጣትን ከከንፈር ትይዩ አድርጎ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | አፍ በመጠኑ ይከፈታል |

### *4. ዘመናዊ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ ‘‘ሀ’’ የግራው ደግሞ ገ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኙ ‘‘ሀ’’ እጅ ከንፈርን አስነክቶ የግራውን ገ እጅ ወደ ላይ |

| | |
|---|---|
| | መቦረሽ |
| የፊት/የሰውነት/ እንቅስቃሴ | አፍ ተገጥሞ በመጠኑ ወደ ፊት ይወጣል |

*5. ራስን መሳት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ ሁለት ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ቀኝ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ግንባር ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በአመልካች ጣት ግንባርን ነክቶ በመገልበጥ በመሀል ጣት ግንባር ላይ ማሳረፍ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ዐይን ይጨፈናል። |

*6. ኢንፌክሽን (ቁስለት)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ የተጨበጠ "9" ቁጥር የግራ እጅ "S" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | በግራ እጅ አይበሉባ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ቁስል እንደመላጥ ዓይነት እንቅስቃሴ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለም |

*7. ደፋር*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ "S" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | "S" እጅን ደረት ላይ ደጋግሞ መታ መታ ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ደረትን ወደ ፊት ገፋ ማድረግ |

*8. ልማድ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ "1" ቁጥር እና "S" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ግንባር ላይ እና ደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ከግንባር ወደ ደረት መውሰድ |

የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ የለም

## ከመልመጃ ስድስት የሚጠበቁ መልሶች

| | ተመሳሳይ | ተቃራኒ |
|---|---|---|
| 1. መውሰድ | መቀበል | መተው |
| 2. በሽተኛ | ህመምተኛ | ጤነኛ |
| 3. መስራት | መተግበር | ቦዘኔ |
| 4. አደገኛ | ከባድ/አስፈሪ | ቀላል/ተለመደ |
| 5. ልማድ | ወግ/ባህል | ያልተለመደ/አዲስ |

### ሃሳብን የመግለጽና የመቀበበል ክሂል

በዚህ ክፍል ትምህርት ተማሪዎች በቡድን የተወያዩበትንና ከተለያዩ ቦታዎች የሰበሰቡትን የውይይታቸውን ውጤት ያቀርባሉ በመሆኑም ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎች ለቀጣይ ሥራ ሙሉ ፍላጎትና የተወዳዳሪነት መንፈስ እንዲሰርጽባቸው ያድርጉ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ተላላፊ በሽታዎች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለ ተላላፊ በሽታዎች ምንነት በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ተላላፊ በሽታዎች እንዴትና በምን ዓይነት መንገድ እንደሚተላለፉ በኢምቋ ይዘረዝራሉ፤
- ራሳቸውን ከተላላፊ በሽታዎች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው በኢምቋ ይዘረዝራላሉ፤
- ተላላፊ በሽታዎች የሚያስከትሉት ማኅበራዊ ጠንቆችን ይለያሉ፤
- ከተላላፊ በሽታዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም ዐ/ነገሮች በምልክት ቋንቋ ሰዋስው ይመሰርታሉ፤
- ከተላላፊ በሽታዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከተላላፊ በሽታዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ ስድስት የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን የተላላፊ በሽታዎችን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በአጠቃላይ የምዕራፉ ሂደት የሚመለሱ ናቸው፡፡ የቅድመ ምንባብ ጥያቄች የቀረበበት ዓላማ ተማሪዎች ስለ ርዕሱ ያለቸውን ዕውቀት ለመገመትና በምን ዓይነት የማስተማሪያ መንገድ ምዕራፉን እንደሚያስተምሩ ለመለየት ነው፡፡

### ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. ጉንፋን ከታማሚው ሰው ወደ ጤነኛ ሰው የሚተላለፈው በትንፋሽ አማካይነት ነው፡፡
2. በውይይቱ ውስጥ የተዘረዘሩት ተላላፊ በሽታዎች ሰባት ሲሆኑ እነሱም ጉንፋን፣ ሳንባ ነቀርሳ፣ ኤችአይቪ/ኤድስ፣ ኢቦላ፣ ኮሌራ፣ ተስቦና ታይፎይድ ናቸው፡፡
3. የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚተላለፈው ቱበርኩሎሲስ በተባለ ባክቴሪያ አማካይነት ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል፡፡
4. የሳንባ ነቀርሳ በሽታን የሚያስተላልፈው ባክቴሪያ ቱበርኩሎሲስ ይባላል፡፡
5. የኢቦላ በሽታ የሚተላለፍባቸው በመንገዶች መነካካት፣ በትንፋሽ፣ በበሽታው የተያዘ ሰው በተጠቀመባቸው ዕቃዎች በመጠቀም ወዘተ ናቸው፡፡
6. ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል የሚቻለው የግልና የአካባቢን ንጽህና በመጠበቅ፣ ንጽህናቸው የተጠበቁ ምግቦች በመመገብ በጉንፋንና በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የተያዙ ሰዎች በሚያስሉበትና በሚያስነጥሱበት ወቅት አፍንና አፍንጫን በመሀረብ በመሸፈን ወዘተ ነው፡፡
7. በውይይቱ ውስጥ የተጠቀሱ በትንፋሽ አማካይነት ከታማሚ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ሦስት ሲሆኑ እነሱም ሳንባ ነቀርሳ ጉንፋንና ኢቦላ ናቸው፡፡

## ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የውይይታቸውን ፍሬ ነገር ለክፍል ተማሪዎች ያቀርባሉ፡፡ የውይይታቸውን ውጤት በሚያቀርቡበት ወቅት የሚያቀርቡትን ገለጻ መሰረት ያደረገ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ ርዕሱ ተጨማሪ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዟቸው፡፡

# ክፍል ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

## ከመልመጃ ሶስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

1. ሱሰኞች ሱሰኛ- ዎች (ሱስ + ጨራሽ + ብዙ)
2. ቃሚዎች ቃሚ- ዎች (ቃሚ + ጨራሽ + ብዙ)
3. አስተላላፊ አስ- ተላላፊ (ተላላፊ + ጨራሽ)
4. በታማኝነት በ- ታማኝ- ነት (ታማኝ + ጨራሽ)
5. ባክቴሪያዎች ባክቴሪያ- ዎች (ባክቴሪያ + ብዙ)

ተመሳሳይ ሆነው ብዛት ያላቸውን ባክቴሪያዎችን ለመግለጽ ባክቴሪያ የሚለውን ምልክትና ብዙ የሚለውን ምልክት መጠቀም ሲቻል የተለያዩ ሆነው ብዛት ያላቸው ባክቴሪያዎችን ለመግለጽ ደግሞ ባክቴሪያ የሚለውን ምልክትና ልዩ ልዩ የሚለውን ምልክት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ቃላት/ምልክቶች የተለያዩ ቅጥያዎች እንዳላቸውና ቅጥያዎችም መነሻ፣ መድረሻ እንዲሁም መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ከላይ የቀረበውን መልመጃና የመልመጃው መልሶች ምሳሌ በማድረግ ይግለጹላቸው፡፡

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

### *1. ባክቴሪያ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ ''B'' የግራ ደግሞ ገ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደታች የግራው ደግሞ ወደ ቀኝ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ/ ከደረት ፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን ''B'' እጅ በአመልካች ጣት በኩል የግራ እጅ መዳፍ አስደግፎ እያወዛወዙ ወደ ፊት ማድረግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *2. ቫይረስ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ እጅ ''V'' የግራው ደግሞ ገ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ታች የግራው ደግሞ ወደ ቀኝ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ/ፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን ''V'' እጅ በአመልካች ጣት በኩል የግራውን እጅ መዳፍ አስደግፎ ወደፊት መወሰድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *3. ቆሻሻ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “5” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | አገጭ ስር |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ጣትን እያርገበገቡ ወደ ግራ መውሰድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *4. ንጽህና/ንጹህ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ታች የግራው ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን እጅ መዳፍ በግራ እጅ መዳፍ ላይ መስቀለኛ አስቀምጦ |

| | |
|---|---|
| | የቀኙን እጅ ብቻ ወደ ፊት መውሰድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*5. መከላከል*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከግራ ትከሻ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም ''S'' እጆች በሰያፍ አጋጥሞ ወደ ግራ መግፋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ይኮሳተራል |

*6.ጥንቃቄ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "T" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ግራ የግራው ደግሞ ወደ ቀኝ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ/ ከደረት ፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱንም "T" እጆች አደራርቦ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ይኮሳተራል |

*7. ሐኪም*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ እጅ "B" የግራው ደግሞ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ታች የግራው ደግሞ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ ሰዓት ማሰሪያ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኙ "B" እጅ የግራ እጅን መገጣጠሚያ በመያዝ ወደ ታችና ወደ ላይ መፈተግ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*8. መድኃኒት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ እጅ "5" ቁጥር የግራው ደግሞ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ታች የግራው ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ መዳፍ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን እጅ የመሀል ጣት የግራ እጅ መዳፍ ላይ አድርጎ ማሽከርከር |

የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ　　　　　የለውም

## ከመልመጃ ስድስት የሚጠበቁ መልሶች

*በተሟላ ሁኔታ በምልክት ቋንቋ ሃሳብን ለመግለጽ ይህንን ክፍለ ትምህርት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎቹን ከመመለሳቸው በፊት ከጥያቄዎቹ በላይ የቀረበውን ገለጻ በጥንቃቄ እንዲያነቡትና ግልጽ ያልሆነላቸው ሃሳብ ካለ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፡፡*

1. በምልክት ቋንቋ ቦታን ለማመልከት የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መጠቆም ነው፡፡ ለምሳሌ በአጠገባችን ያለ ነገርን ለማመልከት ወደ ዕቃው በመጠቆም የምንጠቀም ሲሆን ትንሽ ራቅ ብሎ የሚገኝ ነገርን ለማመልከት ደግሞ ከትከሻችን ትይዩ ያለ ቦታን እንጠቀማለን፡፡

2. በምልክት ቋንቋ አጠገባችን ያለና አጠገባችን የሌለ ነገር ወይም ግለሰብ ለማመልከት የምንጠቀመው የእጅ እንቅስቃሴና የፊት አገላለጽ በመጠቀም ነው፡፡

3. በምልክት ቋንቋ ብዛት ለማመልከት የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች ምልክቱን በመደጋገም፣ ከምልክቱ ቀጥሎ ብዙ የሚለውን ምልክት በመጠቀም የእጅ እንቅስቃሴውን በመደጋገም ነው፡ ፡ ለምሳሌ ሰበረ የሚለው ምልክት ምልክቱ/ድርጊቱ ሲደጋገም ሰባበረ፣ ቆረጠ የሚለው ደግሞ ቆራረጠ፣ ዛፍ የሚለው ምልክት የእጅ እንቅስቃሴው ሲደጋገም ዛፎች ወይም ደን የሚለው ምልክት ይሆናል፡፡

4. በምልክት ቋንቋ የሰዋሰው ሚና የሚጫወቱት ቦታ ጊዜና ብዛት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከፊት ለፊታችን ያለው ቦታ የወደፊት ጊዜንና የትንቢት ጊዜን ያመለክታል ከኋላችን ያለው ቦታ ደግሞ ያለፈ ጊዜን ሲያመለክት ከጎናችን ያለው ቦታን መጠቀም ደግሞ ቀጥሎ /በቅርቡ የሚመጣ/ ጊዜን ያመለክታል፡፡

5. አንድ በምልክት ቋንቋ የሚናገር ሰው የትንቢት ወይም የወደፊት ጊዜን ለማመልከት የሚጠቀመው ቦታ ከፊት ለፊት ያለውን ቦታ ነው፡፡ለምሳሌ ወደፊት፣ ነገ፣ በሚቀጥለው ወዘተ፡፡

### ሀሳብን የመቀበልና የመግለጽ ክህሎት

በዚህ ተግባር የክፍሉ ተማሪዎችን በአራት ቡድን ይክፈሏቸው፡፡ ሶስቱ ቡድኖች በተወካዮቻቸው አማካይነት የተለያዩ ታሪኮችን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ የመጨረሻው ቡድን ደግሞ ሶስቱ ቡድኖች ያቀረቡትን ውይይት ዋና ዋና ሃሳቦች በማስታወሻ በመያዝ የሶስቱን ቡድኖች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ትክክለኛ የቦታ፣ የጊዜና የብዛት አጠቃቀማቸውን እንዲሁም የማስታወሻ አያያዝ ችሎታ እንዲኖራቸው ገለጻ በመስጠት እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# ኤች ኤይ ቪ/ኤድስ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የኤችአይቪ/ኤድስ ምንነት በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ኤችአይቪ/ኤድስ የሚተላለፍባቸውን መንገዶችንና በኤችአይቪ/ኤድስ እንዳንያዝ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- ኤችአይቪ/ኤድስ የሚያስከትለው ማኅበራዊ ጠንቆች ትዘረዝራላችሁ፤
- ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር ተዛማጅነት ያሏቸውን ምልክቶች በመጠቀም በምልክት ቋንቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- የተለያዩ ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር ተዛማጅነት ያሏቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከኤችኤቪ/ኤድስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ ሰባት የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን ኤችኤይቪ/ኤድስን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምንባቡ ውስጥና በምዕራፉ የተለያዩ ክፍሎች የሚመለሱበመሆናቸው ተማሪዎች ስለ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ያላቸው ግንዛቤ ለመገመት የተዘጋጀ ነው፤ በመሆኑም ከምንባቡ በፊት ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በምልክት ቋንቋ ያቅርቡላቸውና ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. የአባላዘር በሽታዎች በዋናነት በሁለት የሚከፈሉ/ የሚመደቡ/ ሲሆን እነሱም በህክምና የሚድኑና በህክምና የማይድኑ ናቸው፡፡
2. በምንባቡ ውስጥ የተዘረዘሩ የአባላዘር በሽታዎች ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም ቂጥኝ፣ ጨብጥ፣ ባምቡሌ/እባጭ/፣ ትሪኮሞኒያሲስ፣ ካንዲዲያሲስ እና ኤችአይቪ/ኤድስ ናቸው፡፡
3. ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመፈጸም፣ አንድ ለአንድ በጋብቻ ተወስኖ መኖር፣ መርፌና ስለታም ነገሮች በጋራ አለመጠቀም፣ ደም በልግስና ከመቀበልና በልግስና ከመስጠት በፊት ከኤችአይቪ ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ኮንዶም በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም፣ የጥርስ በሩሽ የጺም መላጫ የመሳሰሉትን ዕቃዎች በጋራ አለመጠቀም፣ ጎጂ የሆኑ የባህል ህክምና አለመጠቀም፣የጤና አጠባበቅ ትምህርትማስፋፋት፡፡
4. በኤችአይቪ/ኤድስ የተያዘ ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶች የሰውነት ክብደት መቀነስ፣በህክምና ሊድን የማይችል ከወር በላይ የሚቆይ የተቅማጥ በሽታ፤ ከአንድ ወር በላይ የሚቆይ የሰውነት ተኩሳትና የሳል በሽታ፣ የሰውነት ዕጢዎች ማበጥ፣ የሳንባ ምችና የሳንባ ነቀርሳ በሽታዎች መከሰት ወዘተ ናቸው፡፡
5. ኤችአይቪ/ኤድስ ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው የሚተላለፈው በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት ነው፡፡

6. ኤችአይቪ/ኤድስ የማይተላለፍባቸው መንገዶች አብሮ በመመገብ፣ መጸዳጃ ቤት በጋራ በመጠቀም፣ አብሮ በመኖር፣ አብሮ በመጫወት ወዘተ ነው፡፡
7. በኤችአይቪ/ኤድስ ለተያዙ ሰዎች የሚደረግ ህክምና የለም፤ ይሁን እንጂ በቶሎ የኤድስ በሽተኛ እንዳይሆኑ የሚሰጥ መድኃኒት አለ፡፡
8. ለበሽታው መስፋፋት ዋና ዋና ምክንያቶች ሴተኛ አዳሪነት፣ ሥራ አጥነት፣ ስለበሽታው የግንዛቤ እጥረት ወዘተ ናቸው፡፡
9. ኤችአይቪ/ኤድስ በዓለም ላይ የታወቀው እኤአ ከ1981 ዓ.ም ወዲህ ነው፡፡
10. ስለ ኤችአይቪ/ኤድስ የማይተላለፍባቸው መንገዶች የሚናገረው አንቀጽ ሰባት ነው፡፡

## ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

ይህ መልመጃ የውይይት ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት በመሆኑ በሥርዓት ተራ ጠብቀው መወያየታቸውን፣ ከርዕሱ አለመውጣታቸውን፣ ተገቢ የሆነ ምልክት መጠቀማቸውን ይከታተሉ፡፡ በመቀጠልም ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎች የውይይት ጠቃሜታን እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

## ከመልመጃ ሶስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

### *1. ጡት ማጥባት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “1” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | አመልካች ጣትን ወደ ላይ በማድረግ አንገትን ማጎንበስ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | አንገት ወደ ደረት ያዘነብላል አፍ የመጥባት ምልክት ያሳያል |

*2. ጨብጥ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ ጨ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከጆሮ አጠገብ /ጆሮ ግንድ ላይ/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ከጆሮ ግንድ ወደ ጉንጭ ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*3. ቂጥኝ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “ቀ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከጆሮ አጠገብ /ጆሮ ግንድ ላይ/ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ከጆሮ ግንድ ወደ ጉንጭ ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*4. ባምቡሌ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ በ ቁጥር የግራ እጅ ደግሞ 1 ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ አመልካች ጣት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የግራውን አመልካች ጣት በቀኙ በ እጅ በአውራ ጣት በኩል ማከክ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*5. ከርክር*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ በ ቁጥር የግራ እጅ ደግሞ 1 ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ አመልካች ጣት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የግራውን አመልካች ጣት በቀኙ በ እጅ በአውራ ጣት በኩል ማከክ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *6. ህዋስ/ሴል*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ ''C'' የግራ ደግሞ ''S'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ግራ የግራው ደግሞ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ እጅ ክንድ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን ''C'' እጅ የግራ እጅ ክንድ ላይ ወደ ኋላና ወደ ፊት ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *7. ላብራቶሪ/ቤተ ሙከራ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “ለ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | አንድ ዐይን ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም “ለ” በማደራረብ እጆች ዐይን ላይ አድርጎ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | አንደኛው ዐይን ይጨፈናል |

### *8. ግብረሰዶም*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “L” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ቀኝ እጅ ወደ ግራ አቅጣጫ ግራ እጅ ደግሞ ወደ ቀኝ አቅጣጫ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | በደረት ትይዩ አየር ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ቀኝ እጅ ወደ ፊት ወደ ኋላ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለም |

### *9. መጠቀም*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ ''U'' |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*10. መወሰን*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ “5” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ትይዩ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ግንባር ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በአመልካች ጣት ግንባርን ነክቶ የ”ሠ” ወይም “9” ቁጥር ምልክት በመስራት ወደ ደረት ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የየራሳቸውን ጥምር ምልክቶች እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ለኢምቋ ጥምር ምልክቶች ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

1. ቀይ + መክተፍ = ቲማቲም
2. ሴት + ንጉስ = ንግስት
3. ቀይ + መጻፍ = እስኪርብቶ/ብዕር
4. ጥቁር + ስር/በታች/ = ጥላ
5. ዋና + ከተማ = መዲና
6. ወንድ + ማግባት/ቀለበት/ = ባል
7. ሴት + ማግባት/ቀለበት/ = ሚስት
8. ነጭ + ባሪያ + መክተፍ = ነጭ ሽንኩርት
9. ወንድ + ብቻ = ወንደላጤ
10. ሴት + ብቻ = ሴተላጤ

# ምዕራፍ ስምንት

# አካል ጉዳተኝነት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የአካል ጉዳተኝነት ምንነት በኢምቁ ይገልጻሉ፤
- የአካል ጉዳተኝነት ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፤
- የአካል ጉዳተኝነት የሚከሰትበት ምክንያትና አካል ጉዳተኝነት እንዴት መከላከል እንደሚቻል በኢምቁ ይገልጻሉ፤
- ሕብረተሰቡ ስለአካል ጉዳተኝነት ያለውን ግንዛቤ በድራማ (በጭውውት) ያሳያ፤
- ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም በምልክት ቋንቋ ሰዋስው ዓረፍተ ነገሮች ይመሰርታሉ፤
- ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ ስምንት የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን አካል ጉዳተኝነትን ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍል ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምንባቡ ውስጥና በምዕራፉ የተለያዩ ክፍሎች  የሚመለሱ በመሆናቸው ተማሪዎች ስለ አካል ጉዳተኝነት ያላቸው ግንዛቤ ለመገመት የተዘጋጀ ነው፤ በመሆኑም ከምንባቡ በፊት ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በኢምቋ ያቅርቡላቸውና ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. በምንባቡ ውስጥ ሰባት የአካል ጉዳተኝነት ዓይነቶች ተዘርዝረዋል፡፡
2. የአካል ጉዳተኝነት መንስኤዎች ሰው ሰራሽ ጉዳቶች፣ በተፈጥሮ አደጋዎችና ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ አካል ጉዳተኛ ሆኖ መወለድ ናቸው፡፡
3. ተሐድሶ ማለት ለአካል ጉዳተኞች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ጉዳታቸውን ማቃለል ማለት ነው፡፡
4. ከወሊድ በፊት አካል ጉዳተኝነት መከሰት ማለት በእርግዝና ወቅት በእናትየው ላይ በሚከሰት የተለያዩ አደጋዎች አማካይነት፣ በእርግዝና ወቅት አልኮል መጠጥ አብዝቶ በመጠጣት ምክንያት ወዘተ የሚወለደው ልጅ አካል ጉዳተኛ ሆኖ ሲወለድ ማለት ነው፡፡
5. ለአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ፍንዳታ፣ ከከፍተኛ ቦታ መውደቅ፣ የመኪና አደጋ፣ ጎርፍ፣ የእሳት አደጋ ወዘተ ናቸው፡፡

## ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

1. ሐ
2. ሀ
3. ለ
4. መ

## ከመልመጃ ሦስት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ ክፍለ ትምህርት የሚቀርቡ የመወያያ ጥያቄዎች መልስ እንደ በተማሪዎች የቡድን ውይይት ውጤት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓላማ የተማሪዎችን የመወያየት ክሂል ማዳበር ስለሆነ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከተሰጠው የመወያያ ርዕስእንዳይወጡ፣ ተራ ጠብቀው እንዲወያዩ፣ ይንገሯቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

*1. በከፊል ዓይነ ስውርነት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ የታጠፈ “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከዐይን ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የጣቶችን ጫፍ ከዐይን ትይዩ አድርጎ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ማርገብገብ |

| | |
|---|---|
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ዐይን በመጠኑ ይጨፈናል |

*2. ማየትም መስማትም መሳን*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ "ፕ" በግራ እጅ "2" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ቀኝ እጅ ወደ ግራ አቅጣጫ ግራ እጅ ደግሞ ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ግራ እጅ በዐይን ላይ ቀኝ እጅ ደግሞ በጆሮ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ግራ እጅን ከዐይን ላይ አድርጎ ወደ ታች መቆልመም ቀኝ እጅ ከጆሮ ወደ አፍ አምጥቶ አፍ ላይ ማሳረፍ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ዐይን ይጨፈናል |

*3. መናገር/ ማውራት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ የጉርሻ ምልክት |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከአፍ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ከአፍ ትይዩ አድርጎ አውራ ጣትን በሌሎች ጣቶች መጠብጠብ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | አፍ እጅን ተከትሎ ይነቃነቃል |

*4. ችግር*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ ጎርበብ ያሉ "ሸ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ቀኙን ወደ ግራ ግራውን ደግሞ ወደ ቀኝ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | በደረት ፊት ለፊት አየር ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በሁለቱም እጅ በተራ በተራ ክብ መስራት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*5. አእምሮ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ ጎርበብ ያሉ "ሸ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግንባር ጎን ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ላይና ታች ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *6. ተደራራቢ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጆች “ገ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | እያፈራረቁ አንዱን እጅ በሌላው ላይ መጫን |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *7. የጆሮ መርጃ መሳሪያ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ ‘’X’’ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ጆሮ ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የ‘’X’’ እጅ ከጆሮ ኋላ በማድረግ ወደ ላይ መጠምዘዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *8. ተሽከርካሪ ወንበር (ዊልቸር)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጆች ‘’S’’ እና “5” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ትይዩ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ከሆድ ጎንና ጎን እጅን እየጨበጡ /‘’S’’/ ወደ ፊት መዘርጋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### *9. ክራንች /ምርኩዝ/ (በአንድ እጅ በትከሻ ድጋፍ የሚያዝ)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ እጅ ‘’B’’ የግራው ደግሞ ‘’S’’ |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ትከሻ ስር |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን ‘’B’’ እጅ ትከሻ ስር በማድረግ የግራውን ‘’S’’ እጅ ወደታች መጫን |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የእጅ እንቅስቃሴውን ተከትሎ ትከሻ ወደ ጎን ያዘነብላል |

(እንደ የጉዳቱ ቦታ የምልክቱ አቅጣጫ ሊቀየር ይችላል፡፡ ጉዳቱ በግራ እግር ላይ ከሆነ ምልክቱ በግራ በኩል የሚሰራ ሲሆን በቀኝ እግር ላይ ከሆነ በቀኝ በኩል ይሆናል፡፡)

### 10. ነጭ በትር (ኬን)

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “1” ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከሆድ ትይዩ/ ከሆድ ፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | አመልካች ጣትን ወደታች ዘቅዝቆ ወደ ግራና ቀኝ ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ዐይን ይጨፈናል |

## ከመልመጃ ስድስት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች ትክክለኛ የጋዜጠኛና የጤና ባለሙያ፣ የጋዜጠኛና አካል ጉዳተኛ የአካል ጉዳተኛ ቤተሰብና የአካል ጉዳተኛ ጎረቤት ወዘተ ትክክለኛ ባህሪ ወክለው መተወናቸውን፣ ትክክለኛ መልዕክት ማስተላለፋቸውን፣ ትክክለኛ ምልክት ቋንቋ መጠቀማቸውን፣ ተራ ጠብቀው መወያየታቸውን ተመልክተው ለወደፊቱ የተሻለ እንዲሰሩ ግብረ መልስ በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ ሰባት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ መልምጃ ተማሪዎች የተለያዩ መልሶች ሊያቀርቡ ይችላሉ፤ ሆኖም መልሶቹ ከዚህ በታች ካለው ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

1. እሷ ለእኔ ሰጠችኝ (እሷ የሚለውን ምልክት ሰርቶ መስጠት የሚለውን ምልክት ከውጭ ወደ ራስ ማድረግ)
2. እኔ ለእሱ ሰጠሁት( ምልክቱን ከራስ ወደ ውጭ ማድረግ)
3. ከበደ ለጓደኛው ሰጠው ( ጓደኛ የሚለውን ምልክት ካሳዩ በኋላ ከ-በ-ደ የሚለውን በጣት ፊደል አሳይቶ መስጠት የሚለውን ምልክተ ከግራ ወደ ቀኝ መስራት)
4. አልማዝ ለእነሱ ሰጠቻቸው ( አ-ል-ማ-ዝ የሚለውን በጣት ፊደል አሳይቶ መስጠት የሚለውን ምልክት ከግራ ወደ ቀኝ እየደጋገሙ መስራት)
5. መምህሩ ለተማሪዎች ሰጣቸው (መምህር የሚለውንና ተማሪ የሚለውን ምልክት ሰርቶ መስጠት የሚለውን ምልክት እየደጋገሙ መስራት)

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የታዋቂ አርቲስቶች ግለ ታሪክ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የተለያዩ ታዋቂ አርቲስቶች ግለ ታሪክን በመገንዘብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ ይተርካሉ፤
- የአርቲስት ምንነትና ዓይነቶችን በኢምቋ ይገላጻሉ፤
- አርቲስት ለሀገር እድገት ያለው አስተዋጽዖ በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ ያስረዳሉ፤
- የመስማት የተሳናቸው አርቲስቶች ግለ ታሪክ ያቀርባሉ፤
- ከአርትና ከአርቲስት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች በምልክት ቋንቋ ሰዋስው ይመሰርታሉ፤
- ከአርትና ከአርቲስት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ተፈጥሮን ከአርቲስት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን የታዋቂ አርቲስቶች ግለ ታሪክን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍል ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

### ቅድመ ምንባብ

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምንባቡ ውስጥና በምዕራፉ የተለያዩ ክፍሎች  የሚመለሱ በመሆናቸው ተማሪዎች ስለ ታዋቂ አርቲስቶችና የጥበብ ሥራዎቻቸው ያላቸው ግንዛቤ ለመገመት የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም ከምንባቡ በፊት ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በምልክት ቋንቋ ያቅርቡላቸውና ተማሪዎች ስለ ታዋቂ አርቲስቶችና የጥበብ ሥራዎቻቸው የሚያውቁትንና የመሰላቸውን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልምጃ አንድ የሚጠበቁ መልሶች

1. የዓለም ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ የተለያዩ የሥነ ጥበብ ሥራዎች ማለትም የስእል ሥራ፣ የመስታወት ሥራ፣ የቀለም ቅብ፣ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ሰርተዋል፡፡
2. በውጭ ምንዛሬ ሦስት መቶ ሺህ ብር አልሸጥም በማለት ለትውልዱ ያስተላለፉት ስዕል "የመስቀል አበባ" ይባላል፡፡
3. አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በሥነ ጥበብ ሥራዎቻቸው  ለሀገራችን በበርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ማስገኘታቸው፣ ጨረቃ ላይ የኢትዮጲያ ባንዲራ እንዲሰቀል ማድረጋቸው፣ የአክሱም ሐውልት አስመላሽ ኮሚቴ ሆነው ሐውልቱ እንዲመለስ ማድረጋቸው፣ አፍሪካውያን ይደርስባቸው የነበረውን ጭቆና በስእል ስራዎቻቸው ለዓለም ህዝብ ማሳወቃቸው ናቸው፡፡
4. የዓለም ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የምህንድስናና የቋንቋ ትምህርታቸውን ያቋረጡበት የሥነ ጥበብ ትምህርት በመጀመራቸው ምክንያት ነው፡፡
5. የዓለም ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት በተወለዱበት የአንኮበር ከተማ ነው፡፡
6. አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ በልጅነት ጊዜያቸው የስዕል ችሎታቸውን የሚገልጹት በመማሪያ ደብተራቸው ላይ፣ በወረቀት ላይ፣ በግድግዳ ላይ ወዘተ የተለያዩ ስእሎችን በመሳል

ነበር፡፡

7. የዓለም ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ በ 1954 ዓ.ም አፍሪካውያን ለነጻነታቸው የሚያደርጉትን ትግል ስለዋል፡፡

8. የዓለም ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ በመጀመሪያ የራሳቸውን አውደ ርዕይ (ኤግዚብሽን) የከፈቱት በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ነበር፡፡

## ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶቸ

1. አርት ማለት የእንግሊዘኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ጥበብ ማለት ነው፡፡
2. አርቲስት የተለያዩ የጥበብ ሥራዎችን የሚሰራ ግለሰብ ማለት ነው፡፡
3. በአርት ወይም በአርቲስት ውስጥ የሚመደቡት ሰአሊ፣ ቀለም ቀቢ፣ ዘፋኝ፣ ተወዛዋዥ፣ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች ናቸው
4. አርት ወይም የጥበብ ሥራ ለሀገርና ለግለሰብ የሚሰጡት ጠቃሜታዎች የገቢ ምንጭ ያስገኛሉ፣ ለመዝናኛነት ያገለግላሉ፣ የሀገር ፍቅር ይጨምራሉ፡፡
5. አርቲስት ህዝቡ የሀገር ፍቅር እንዲኖራቸው የሚያደርጉት በጥበብ ሥራዎቻቸው በማስደሰት፣ ስለ ሀገር ፍቅር በመዝፈን፣ በቅርጻ ቅርጽ ስራዎቻቸው ታሪክ በማስተላለፍ ወዘተ ነው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

## ከመልመጃ ሦስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

1. *መቀባት*

1.1. *መቀባት (ለቤት ቀለም)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በአንድ እጅ “B” |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከፊት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ታችና ወደ ላይ ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 1.2. *መቀባት (ለስዕል)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | እጅ "U" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ታችና ወደ ላይ ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

### 1.3. *መቀባት (የጫማ ቀለም)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ "S" የግራ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደታች የግራው ደግሞ ወደ ላይ ከክንፈር ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኙ "S" የግራ እጅን መዳፍ መቦረሽ |
| የሰውነት እንቅስቃሴ | አንገት እጅን ተከትሎ ይወዛወዛል |

### 1.4. *መቀባት (የጸጉር ወይም የሰውነት ቅባት)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "5" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ትይዩ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም እጆች በመዳፍ በኩል አጋጥሞ ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

(ቅባቱ የፊት ከሆነ ከምልክቱ በኋላ ፊትን መዳበስ፣ የጸጉር ከሆነ በተመሳሳይ ጸጉርን መዳበስ ያስፈልጋል)

## *2. መደነስ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኙ እጅ "V" የግራው ደግሞ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ውስጥ የግራው ደግሞ ወደ ላይ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |

| | |
|---|---|
| የእጅ እንቅስቃሴ | የቀኙን "V" እጅ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ማወዛወዝ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት "ጠ" እጅ እንቅስቃሴን ተከትሎ ይወዛወዛል |

*3. ስዕል*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የቀኝ እጅ "ǀ" የግራ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በቀኙ "ǀ" እጅ የግራ እጅ መዳፍ ላይ እያርገበገቡ ወደታች ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

*4. መዝናናት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "5" ቁጥር |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ቀኝ እጅ ወደ ግራ አቅጣጫ ግራ እጅ ደግሞ ወደ ቀኝ አቅጣጫ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | በደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ጣቶችን ማርገብገብ |
| የሰውነት እንቅስቃሴ | የለውም |

*5. ቅርጻ ቅርጽ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "ቀ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጆች ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱንም ቀ እጆች ከደረት ትይዩ አድርጎ እያንቀጠቀጡ ወደታች ማውረድ |
| የሰውነት እንቅስቃሴ | የለውም |

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

በዚህ መልመጃ ምልክቶች ያላቸውን አገባባዊ ትርጉም ተማሪዎች የዓረፍተ ነገሩን ሃሳብ ከተረዱት ምልክቶችን ራሳቸው ሊያሳዩ ስለሚችሉ እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር የያዘውን ሃሳብ ግልጽ ያድርጉላቸው።

## ከመልመጃ ስድስት የሚጠበቁ መልሶች

የዚህ መልመጃ ዓላማ ተማሪዎች እንዴት መረጃ ከየት እንደሚያገኙ፣ እንዴት እንደሚሰበስቡና እንዴት በምልክት ቋንቋ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ስለሆነ መልመጃው የተያዘለት ዓላማ ከግብ ይደርስ ዘንድ አንዳንድ ምሳሌዎችን በመስጠት እንዴት እንደሚሰሩ ያሳዩዋቸው፡፡

# ምዕራፍ አስር

# ሥነ ግጥም

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የግጥም ምንነትና አበይት ባህርያት በኢምቋ ይገልጻሉ፤
- በልሳን ቋንቋና በኢምቋ ግጥሞች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
- የተለያዩ ግጥሞችን በኢምቋ ያቀርቡላችኋል፤
- የግጥም ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፤
- ከግጥም ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች በምልክት ቋንቋ ሰዋስው ይመሰርታሉ፤
- ከግጥም ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች ይተነትናሉ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ: ቁልፍ ምልክቶች

ይህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከስነ ግጥም ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምልክቶችን የሚለማመዱበት ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በምዕራፍ አስር የቀረቡትን ምልክቶችንና ሌሎች የሚውቋቸውን ስነ ግጥምን የሚገልጹ ምልክቶችን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ምልክቶችን በሚያሳዩበት ጊዜ የምልክቱን የእጅ ቅርጽ፣ የመዳፍ አቅጣጫ፣ የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፣ የእጅ እንቅስቃሴውን፣ የፊትና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በሚገባ ይከታተሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ማዳመጥ (መመልከት)

**ቅድመ ምንባብ**

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች መልስ በምዕራፉ የተለያዩ ክፍሎች የሚመለስ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚያውቁትንና የመሰላቸውን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ ሁለት የሚጠበቁ መልሶች

1. ግጥም በተመረጡ ቃላት ወይም ምልክቶች አድምቆና አጉልቶ መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ ነው፡፡
2. የምልክት ቋንቋ ግጥም በተመረጡ ውበት ባላቸው ምልክቶች የሚቀርብ ሲሆንየልሳን ቋንቋ ግጥም ደግሞ በተመረጡ ቃላት መቅረቡ ነው፡፡
3. የምልክት ቋንቋና የልሳን ቋንቋ ግጥሞች ተመሳሳይነታቸው ሁለቱም መልዕክት ማስተላለፊያ መሆናቸው ነው፡፡
4. ግጥም በምልክት ቋንቋ መግጠም የሚቻለው ውበት ያለው የምልክት፣ የምናብ ምልክቶች በመጠቀም መልዕክት ማስተላለፍ ሲቻል ነው፡፡
5. የምልክት ቋንቋ ግጥም ባህርያት ግልጽና በቀላሉ የሚታይ ምልክት መጠቀም፣ ልዩ የቋንቋ ክሂል መኖር በሰውነት እንቅስቃሴያ መልዕክት ማስተላለፍ መቻል፣ የምልክት ቋንቋ ማህበረሰብ ባህል ማወቅ፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የምልክት አገላለጾችን በሚገባ ማወቅ፣ ተገቢና ምክንያታዊ የሆነ የፊት እንቅስቃሴ መጠቀም ናቸው፡፡
6. ከምልክት ቋንቋ በተጨማሪ የማህበረሰቡን ቋንቋና ባህል በሚገባ ማወቅ ስፈልጋል፡፡ ከላይ ለጥያቄ አምስት የቀረበውን ማብራሪያ ማወቅ እጅግ ይጠቅማል፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሶስት፡ መናገር (መግለጽ)

### ከመልመጃ ሦስት የሚጠበቁ መልሶች

መምህር በዚህ መልመጃ ላይ ተማሪዎች የተሰጧቸውን ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላትን በመጠቀም የየራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲገነቡ ያበረታቷቸው፡፡

### ከመልመጃ አራት የሚጠበቁ መልሶች

1. *ደስታ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | ሁለቱንም እጅ መዘርጋት (በሁለቱም እጅ ገ) |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጅ ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ላይ ደረትን በመዳፍ መቦረሽ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ፈገግ ይላል |

2. *ሀዘን*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ የተጨበጠ (''S'') |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | የግራ ደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ማሽከርከር |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ይጨፈግጋል (የሀዘን ምልክት ማሳየት) |

3. *ሲነፃበብ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ "ገ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የሁለቱም እጅ ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ደረት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ላይ ደረትን በመዳፍ መቦረሽ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | ፊት ፈገግ ይላል |

4. *ምኞት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በሁለቱም እጅ አመልካች ጣት (“1” ቁጥር) |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | አንገት ላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ታችና ወደላይ እያፈራረቁ ማውጣትና ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | አንገት ወደ ላይ ቀና ይደረጋል |

5. *ሲያሜ (ብያኔ)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የሁለትም እጅ የተገጠመ አመልካችና የመሃል ጣት (“ሀ”) |
| የመዳፍ አቅጣጫ | የቀኙ ወደ ግራ የግራው ደግሞ ወደ ውስጥ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ፊት (ከደረት ትይዩ) |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ሁለቱን ጣቶች በሰያፍ በማደራረብ ከደረት ትይዩ አድርጎ ወደ ፊት መግፋት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለውም |

6. *አግዝፎ (አተልቆ)*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የሁለቱንም እጅ አመልካችንና አውራ ጣትን መዘርጋት (“L”) |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ትይዩ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | የሁለቱንም እጅ አውራ ጣትንና የአመልካች ጣትን አጋጥሞ ማለያየት |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | እንደ ግዝፈቱ መጠን የፊት እንቅስቃሴ ይለያያል |

7. *ሁኔታ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የሁለቱም እጅ ጎርበብ ያለ "ሸ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ቀኝ እጅ ወደ ግራ አቅጣጫ ግራ እጅ ደግሞ ወደ ቀኝ አቅጣጫ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት በላይ |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ግማሽ ክብ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለም |

8. *ቅርጽ*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | በቀኝ እጅ "አ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ግራ አቅጣጫ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ፊት ለፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | በማንቀጥቀጥ ወደታች ማውረድ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለም |

9. *ድርጊት*

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ | የሁለቱም እጅ "ከ" |
| የመዳፍ አቅጣጫ | ወደ ታች |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ | ከደረት ፊት ለፊት |
| የእጅ እንቅስቃሴ | ወደ ፊትና ወደኋላ |
| የሰውነት/የፊት እንቅስቃሴ | የለም |

## ከመልመጃ አምስት የሚጠበቁ መልሶች

ተማሪዎች በቡድን ሆነው ይሰሯቸዋል ተብለው የሚጠበቁ መልሶች፣

1. በአንድ ቁጥር የእጅ ቅርጽ የሚሰሩ ምልክቶች፡

አይቻልም፣ አሰልቺ፣ ጥቁር፣ ውሸት፣ አውነት፣ ነው፣ ሐሺሽ፣ ልማድ፣ አጢኃት፣ መናገር. . . ወዘተ ናቸው፡፡

እነዚህንና ሌሎችንም በአመልካች ጣት ብቻ የሚሰሩ ምልክቶችን በማቀናጀት ተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡

2. በአምስት ቁጥር የእጅ ቅርጽ ሊሰሩ የሚችሉ ምልክቶች፡

ማጨብጨብ፣ እልልታ፣ ሰልፍ፣ ቀላል፣ ሳር፣ ሰርግ፣ ማሸብሸብ፣ ዝናብ፣ ዛፍ፣ እስር ቤት፣ አጥር፣ አባት፣ እናት . . . ወዘተ ናቸው፡፡

3. በ "ገ" የእጅ ቅርጽ ለሰሩ የሚችሉ ምልክቶች፣

ጋምቤላ፣ ገዳም፣ ጉልላት፣ ገጠር፣ ማጨድ፣ ደስታ፣ እግዚአብሔር፣ ገነት፣ ጎጃም፣ ጎንደር፣ ግማሽ፣ ማገልገል፣ ግጥም. . . . . ወዘተ ናቸው፡፡

4. በ "ሠ" የእጅ ቅርጽ ሊሰሩ የሚችሉ ምልክቶች፣

ሻይ፣ ወጥ፣ ጫት፣ ድመት፣ መስፋት (ለእጅ ስፌት ብቻ)፣ ፋብሪካ፣ አስፈላጊ (important የሚለውን ለመግለጽ)፣ ማስቲካ . . . ወዘተ ናቸው፡፡

5. በተጨበጠ እጅ ወይም በ "S" የእጅ ቅርጽ ሊሰሩ የሚችሉ ምልክቶች፣

መጣላት፣ መከላከል፣ ሞተር ሳይክል፣ ጫማ፣ ሥራ፣ ደደብ፣ ማዘን፣ መወዳደር፣ ዳቦ፣ መዳን፣ መስበር፣ መኪና . . . . ወዘተ ናቸው፡፡

## ከመልመጃ ስድስት የሚጠበቁ መልሶች

ተማሪዎችን በቡድን ተከፋፍለው እንደ ቡድናቸው ከተራ ቁጥር ከ "1-10 "፣ ከ ሀ- አ፣ ከ ኩ-ፐ ባሉ የጣት ፊደሎች የኢምቁ ምልክቶችን ወይም ምናባዊ ምልክቶችን (classifiers) ሰብስበው በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጉ በመቀጠልም የጻፏቸውን ምልክቶች በማጣመር የተለያዩ መልዕክት ያላቸው ጭውውቶችን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በዚህም ዐውድ የምልክት አጠቃቀማቸውን፣ የፊት እንቅስቃሴአቸውን፣ የተሟላ መልዕክት ማስተላለፋቸውን ይገምግሙና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 7ኛ ክፍል

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር